# በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ (በሞረትና ጅሩ ወረዳ 9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በከፊል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

በ


አላዩ ደሳለኝ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ፡- አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


ጥቅምት 2014ዓ.ም

ጅማ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ፡- አማርኛ ትምህርት ክፍል

# በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ (በሞረትና ጅሩ ወረዳ 9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በከፊል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሑፍ

በ

አላዩ ደሳለኝ

የጥናቱ አማካሪዎች

ዋና አማካሪ፡-ማንያለው አባተ(ዶ/ር )

ረዳት አማካሪ፡- ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

ጥቅምት 2014 ዓ.ም

ጅማ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ፡- አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

### በፈታኞች ቦርድ አባላት የቀረበ ማረጋገጫ

ይህ “ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ” በሚል ርዕስ በከፊል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ አላዩ ደሳለኝ ያቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ  የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

### የፈታኞች ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ----------------------------------------ፊርማ -------------ቀን --------------

የውስጥ ፈታኝ ስም ----------------------------------ፊርማ -------------ቀን -------------

የውጭ ፈታኝ ስም -----------------------------------ፊርማ -------------ቀን ------------

# በአጥኚው የቀረበ ማረጋገጫ

ይህ “በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ” በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርስቲ፣የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ፣አማርኛ ትምህርት ክፍል በከፊል ለሁለተኛ ዲግሪ  ማሟያ ያቀረብኩት ጥናታዊ ፅሁፍ፣ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ፣ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን እና የተጠቀምኩባቸውን  ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የሆኑና ጅማ ዩንቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አላዩ ደሳለኝ

ፊርማ----------------

ቀን------------------

# ምስጋና

በቅድሚያ ለኃያሉ አምላክ ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን፡፡በመቀጠል ጥናቱ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን ሰጥተው ከትልመ ጥናቱ እስከ አጠቃላይ ረቂቁ ድረስ እርማት በመስጠትና ምክር በመለገስ ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለዋና አማካሪዬ ለዶ/ር ማንያለው አባተ እና ለረዳት አማካሪዬ ለዶ/ር ጥበቡ ሽቴ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

እንዲሁም ለጥናቱ መረጃዎችን እሰበስብ ዘንድ በቀናነት ለተባበሩኝ ለእነዋሪ ሚሊኒየም መሰናዶ እና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ለጅሁር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ፣ለዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራንና ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እና ውድ ጊዜዋን ሰውታ የፅሁፍ ስራውን ላገዘችኝ ለወ/ሮ እታለማሁ ንጉሴ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ፡፡እንዲሁም ደግሞ በአራት ዓመት የትምህርት ቆይታዬ ደከማኝ ሰለቸኝ ሳትል የሞራል ድጋፍ ላደረገችልኝ ለውድ ባለቤቴ ለወ/ሮ ሰላማዊት አፈሻ እና ለልጆቼ ለበእምነት አላዩ እና ለቃልኪዳን አላዩ ምስጋናዬ የላቀ ነው ፡፡በመጨረሻም ለጥናቱ ለሚያስፈልገኝ ወጪ መሸፈኛ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አህፅሮተ ጥናት

ይህ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል አቀራረብና የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ በሚል ርእስ የተጠና ሲሆን የጥናቱ ዓላማም በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና የክፍል ውስጥ አተገባበር መገምገም ነው፡፡ለዚህም ጥናቱ አይነታዊ ምርምርን በዋናነት መጠናዊ ምርምርን በደጋፊነት ተጠቅሟል፡፡ተጠኝዎቹም በእነዋሪ ሚሊኒዬም መሰናዶ እና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣በጅሁር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ያሉትን ሁለት ወንድ መምህራንና ሁለት ሴት መምህራንን በድምሩ አራት መምህራንን በጠቅላይ ንምና ዘዴ በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡እንዲሁም ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች ወንድ 150 ተማሪዎች እና ሴት 172 ተማሪዎች በድምሩ 322 ተማሪዎች በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ በመጠቀም ተመርጠው የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል ፡፡ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት የዋለው በዋናነት የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲሆን መረጃውን የበለጠ ተአማኒት እንዲኖረው ከምልከታ በተጨማሪ የመምህራን ቃለመጠይቅና የፅሁፍ መጠይቅ ፣የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሁም ሰነድ ፍተሻ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡የተሰበሰቡት መረጃዎችም ከመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ፣ልምምድ፣አፍልቆትና ምጋቤ ምላሽ አንፃር ተተንትነዋል፡፡የጥናቱ ውጤትም መምህራን ለደረጃው በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችን መሰረት በማድረግ እንደሚተገብሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን አንዳንድ ቦታዎች ላይ የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያላገናዘበ ይዘቶች እንዳሉት ለመረዳት ተችሏል፡፡እንዲሁም መምህራን ለመናገር ክሂል ትምህርት ሰፊ ትኩረት ያለመስጠት እና ይዘትን በመመረጥ የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያማከለ ያለመሆን፣ተማሪዎች ልምምድ ካደረጉ በኋላ ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲናገሩ የማነሳሳቱን ተግባር ባለመወጣታቸው የመናገር ክሂል በሚፈለገው ደረጃ እንዳልደረሰ ጥናቱ አመላክቷል፡፡በመጨረሻም ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች ተገልፀዋል፡፡

# የይዘትማውጫ

ርዕስ ገፅ


ምስጋና ....... II

አህፅሮተ ጥናት ....... III

የይዘትማውጫ ....... III

የሰንጠረዥ ማውጫ ....... vii

ምዕራፍ አንድ ....... 1

መግቢያ ....... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ....... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ችግር ....... 3

1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ....... 3

1.4. የጥናቱ ዓላማ ....... 4

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ....... 5

1.6 የጥናቱ ወሰን ....... 5

ምዕራፍ ሁለት ....... 6

የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ....... 6

2.1. የመናገር ክሂል ምንነት ....... 6

2.2 የመናገር ክሂልን የማስተማር ዓላማ ....... 8

2.3. የቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ....... 10

2.4. የመናገር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት ....... 11

2.5. ተግባቦታዊ አቀራረብ የመናገር ክሂልን ለማስተማር ያለው ድርሻ ....... 12

2.6. የመናገር ክሂልን ለማስተማር የስነ-ፅሑፍ ሚና ....... 13

2.7. የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የመምህራን ተግባራት ....... 14

2.8. የመናገር ክሂልን በመማር ሂደት የተማሪዎች ተግባር ....... 15

2.9. የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት ....... 15

2.9.1 ስዕሎችን በንግግር መግለጽ፡- ....... 15

2.9.2. ልዩነትን በንግግር መግለጽ፡- ....... 16

2.9.3. ተመሳሳይነትን በንግግር መግለጽ፡- ....... 16

2.9.4 ችግርን የመፍታት ተግባራት፡- 16

2.9.5. ታሪክ መናገር፡- 16

2.9.6 ሚና ጨዋታ፡- 17

2.10. ንግግርን የማስተማር ሂደት 18

2.10.1. የቅድመ ንግግር ተግባራት 18

2.10.2. የንግግር ተግባራት 19

2.10.3. የድህረ ንግግር ተግባራት 19

2.11. የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ደረጃዎች 19

2.11.1. አቀራረብ (traditional present) 19

. 2.11.2. ልምምድ (practice ) 20

2.11.3. አፍልቆት (produce) 20

2.11.4. ምጋቤ ምላሽ(feed back) 21

2.12. የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች 21

2.13. የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የሚያዙ ተግባራት 22

2.14. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 24

ምዕራፍ ሶስት 27

የአጠናን ስነ-ዘዴ 27

3.1.የጥናቱ ንድፍ 27

3.2 የመረጃ ምንጮች 27

3.3 የናሙና አወሳሰድ ስልት 27

3.3.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ 27

3.3.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ 28

3.3.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ 28

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 29

3.4.1. ሰነድ ፍተሻ 29

3.4.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ 29

3.4.3 የጽሁፍ መጠይቅ 30

3.4.4 ቃለ መጠይቅ 31

3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት 31

3.6. የመረጃ መተንተኛ ስልት ..................................................31
ምዕራፍ አራት ..................................................33
የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ ..................................................33
4.1. የመምህራን አጠቃላይ መረጃ..................................................33
4.2. ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ትንተና..................................................34
4.3. የመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር መረጃ ትንተና..................................................37
4.4. በክፍል ውስጥ በሚቀርበው የመናገር ትምህርት ልምምድ ጊዜ የመምህሩ ተግባር 46
4.5 የአፍልቆት ደረጃ ክንውኖች የመረጃ ትንተና ..................................................53
4.6. የመናገር ክሂል ትምህርት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ክንውኖች ትንተና ..................................................59
4.7. የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ..................................................63
ምዕራፍ አምስት..................................................65
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳቦች ..................................................65
5.1.ማጠቃለያ ..................................................65
5.2. የመፍትሄ ሐሳቦች..................................................67
አባሪዎች..................................................73
አባሪ አንድ..................................................73
አባሪ ሁለት..................................................77
አባሪ ሶስት..................................................80
አባሪ አራት..................................................84

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ አንድ ፡- የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ የዘጠኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ------------------------------------------------------------------33

ሰንጠረዥ ሁለት ፡- የመምህሩ/ሯ/ የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በምልከታ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ----------------------38

ሰንጠረዥ ሶስት- የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ተግባራት አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎችን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ------------41

ሰንጠረዥአራት ፡- የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብን በሚመለከት የመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ ምላሽ ትንተና---------------------------------------------44

ሰንጠረዥ አምስት፡- በተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራት ልምምድ ጊዜ

የመምህሩን ሚና በተመለከተ በምለተከታ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ-------47

ሰንጠረዥስድስት፡ የመምህራን የማለማመድ ክንውኖችን በተመለከተ የመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ ምላሽ ትንተና ------------------------------------------------------------------49

ሰንጠረዥ ሰባት፡- በልምምድ ደረጃ የመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ትንተና -------------------------------------------51

ሰንጠረዥ ስምንት፡- የመምህራንን የአፍልቆት ደረጃ ክንውኖች በምልከታ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ -------------------------------------------------------------53

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- በአፍልቆት ደረጃ የመናገር ክሂል ትምህርት በሚመለከት የመምህራንን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ---------------------------------------------56

ሰንጠረዥ አስር፡ በአፍልቆት ደረጃ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በሚመለከት የተማሪዎችን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠዥ------------------------------58

ሰንጠረዥ አስራ አንድ፡- :-የመምህራንን በክፍል ውስጥ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በምልከታ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ--------------------- 60

ሰንጠረዥአስራ:ሁለት በክፍል ውስጥ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ የመምህራንን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ------------------------------- 61

ሰንጠረዥ:አስራ ሶስት: በክፍል ውስጥ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት የተማሪዎችን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ--------------------------------62

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

መናገር የሰው ልጆች ከእንስሳት ከሚለዩበት ባህሪያት አንዱና ዋነኛው ሲሆን የጽሁፍ ጥበብ ከመጀመሩ በፊት ለረጅም ዘመናት ከሰው ልጆች ጋር አብሮ ኖሯል፤አሁንም፣ ወደፊትም አብሮን ይኖራል፡፡ ይሁን እንጂ ንግግር እጅግ ዘግይቶ ከመጣው ከጽህፈት ጋር ሲነጻጸር የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛነው በማለት (Mcdonogh and Shaw ,1995) ገልጸዋል፡፡

እንደ Bygate (1987) አገላለጽ የመናገርን ክሂል ትምህርት አስፈላጊነትን እንዲህ ሲሉ ያስረዳሉ::ሰዎች በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር በሚያደርጉት ንግግርእለታዊ ተግባሮቻቸውን ማከናወን ይችላሉ፡፡በተግባቦቱምጓደኝነት ሊመሰርቱ ወይም ሊያጡ ይችላሉ::አመርቂ የሆንግግር ማህበራዊ ትብብር፣ ማህበራዊ ቦታ፣ሙያዊ ከበሬታ መመስረቻ መንገድ ይፈጥራል፡፡ይህም መናገርን የማስተማር ተገቢነትን ያጎላል፡ተማሪዎች የመናገር ክሂል መማራቸው በክፍል ውስጥ ለሚያቀርቡት ንግግር መረጃ በማሰባሰብና ልምምድ በማድረግ ሀሳባቸውን አደራጅተው መናገር እንዲችሉ እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

ማረው (200፣105)“የመናገር ክሂልን በቋንቋ ትምህርትውስጥ እንደ አንድ ይዘት ማካተት አስፈላጊ እንዳልሆነ ለበርካታ አመታት ይታመን ነበር፡፡ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በብዙ ጥናቶች እንደተረጋገጠው ከቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መካከል አንደኛው የመናገር ክሂል ነው፡፡”በማለት ገልፀዋል፡፡

እንዲሁም Grant(1987) “የመናገር ክሂል በየትኛዉም አካባቢ ከፍተኛ አገልግሎት እንዳለው ቢታወቅም ቋንቋን በመማር ማስተመር ሂደት ግን እንደማዳመጥ ክሂል ትምህርት የተዘነጋ የቋንቋ ትምህርት ነዉ” በማለት ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህም የመናገር ክሂልን ለማዳበር እና ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶት በመርሃ ትምህርቱ፣ በመምህሩ መምሪያና በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መቅረብ የሚገባዉ

ጉዳይ ነዉ፡፡ መናገርን የማስተማሩ ዋናዉ ዓላማም ተማሪዎች በመናገር ብቃት እንዲኖራቸው፣ ትክክለኛና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ ለማስቻል ነዉ፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ሲሆን አይታይም፡፡

የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ ከመምህር መር የማስተማር ተግባር ይልቅ ቡድኖችን በማደራጀት ማስተማር ውጤታማ እንደሆነ (Bygate ,1987) ገልጸዋል፡፡

Ur (1996) በበኩላቸው የክፍል ውስጥ መስተጋብራዊ ክንውኖች አነሳሽነት ሁል ጊዜ በመምህሩ እጅ መውደቅ የለበትም፡፡ መስተጋብሩ በተማሪዎች መካከል ወይም በተማሪዎች እና በመማሪያ መጻህፍቱ መካከል ሊሆን እንደሚገባ  የቋንቋ ክፍልን ገጽታ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን ለመግለጽ እንደተሞከረው የመናገር ክሂል ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለመመስረት፣ እለታዊ ተግባሮችን ለማከናወን ጉልህ ድርሻ የሚያበረክት ቢሆንም ክሂሉን ለማዳበር የሚረዱ ተግባራትን በማስተማሪያ መሳሪያዎች በማካተትም ሆነ የክፍል ውስጥ አተገባበሩን በሚመለከት ብዙም ትኩረት ሳይሰጠው እንደቆየ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ እንደዚህ አይነት ችግሮችን ለመቅረፍ የመምህራን የመናገር ክሂል ይዘቶችን አቀራረብ እና የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል መገምገም ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ይህ ጥናት የተካሄደው በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ በማተኮር ነው፡፡የዚህ ጥናት አጥኚም በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በሞረትና ጅሩ ወረዳ በሚገኙ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና የክፍል ውስጥ አተገባበር መነሻ በማድረግ መገምገም ነው ፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ችግር

የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት የአጥኚው የስራ ላይ ገጠመኝ ነው፡፡ ይኸውም አጥኚው በሞረትና ጅሩ ወረዳ ልዩ ስሙ እነዋሪ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚያስተምርበት ወቅት ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በንግግር ክሂል ከሚያሳዩት ደካማ ግብረ መልስ በመነሳትና መምህራን በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የመናገር ክሂል ይዘቶች በአግባቡ አለመተግበራቸውን መገንዘብ ችሏል፡፡

ስለሆነም ብዙዎቹ ተማሪዎች ስላዳመጡት፣ ስላዩትና ስለተሰማቸዉ ነገሮች የመናገር ችሎታቸዉ ደካማ ስለመሆኑ በየጊዜዉ በክፍል ዉስጥና ከክፍል ዉጪ ከሚያደርጓቸዉ ተግባቦታዊ ችሎታ በመነሳት ያለባቸዉን ክፍተት አጥኚዉ ለመረዳት ችሏል፡፡ለምሳሌ፡- በክርክር ጊዜ፣ በውይይት ጊዜ እና በጭውውት ጊዜ የሚያደርጓቸው ቃል ምልልሶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

እንዲሁም አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት እስከ 1970ዎቹ ድረስ በበርካታ አገሮች ቋንቋን ማስተማር በሰዋሰው፣ በማንበብ እና በመፃፍ ላይ ያተኮረ ነበር:: ከ1970ዎቹ ወዲህ የመናገር ክሂል እንደ አንድ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ቢካተትም ትርጉም ባለው መንገድ ይቀርብ ነበር ለማለት አያስደፍርም(Scrivener,1994)በማለት ገልፀዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብና የክፍል ውስጥ አተገባበርን መገምገም አስፈላጊ መሆኑን አጥኚው ስላመነበት ነው፡፡ ጥናቱም የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

## 1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

አጥኚው በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ሞረት እና ጅሩ ወረዳ የሚገኙትን እነዋሪ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ እና ጅሁር አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚተገብሩት

እና በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶችን አቀራረብ ለመገምገም ሞክሯል፡፡ ጥናቱም የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

- በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት የመናገር ክሂል ይዘቶችና ተግባራት የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘቡ ናቸው?
- መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የሚረዱ ምን ምን ተግባራትን ይጠቀማሉ?
- የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት መምህራን ምን ምን ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ?
- መምህራን የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚተገበሩበት ወቅት አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ ዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን መገምገም ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

- በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት የመናገር ክሂል ይዘቶችና ተግባራት የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘቡ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
- መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የሚረዱ ምን ምን ተግባራትን እንደሚጠቀሙ መገምገም፡፡
- የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት መምህራን ምን ምን ሁኔታዎችን እንደሚያመቻቹ መገምገም፡፡
- መምህራን የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ መለየት፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ ጥናቱ **ለተማሪዎች**፡- ወደፊት በሚኖራቸው ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ሀሳባቸውን በተገቢው መንገድ እንዲገልጹ ሊያግዛቸው ይችላል፤

**ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን**፡- የመናገር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ የተለያዩ ተግባራትን ለይተው በማወቅ በመማር ማስተማሩ ተግባር በቀጣይ እንዲገለገሉባቸው ሊረዳቸው ይችላል፤

**ለመርሃ ትምህርት ንድፈ ቀረፃ ባለሙያዎች**፡- በአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል ትምህርትን ለማስተማር ለስነ ዘዴ መረጣና ለአተገባበሩ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጡ ሊረዳቸው ይችላል፡፡

**እንድሁም ጥናቱ ለሌሎች ተመሳሳይ ጥናቶች ያለው አስተዋፅኦ**፡- በዋናነት በተመሳሳይ ርዕስ ለሚካሄዱ ጥናቶች የመነሻ ሀሳብና በምርምር ሂደቱም የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የተከናወነው በ2013 ዓ.ም በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ሞረትና ጅሩ ወረዳ ስር በሚገኙ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ተማሪዎች ላይ ብቻ በማተኮር ነው፡፡ በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡትን የመናገር ክሂል ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን መገምገም ነው፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ ለመናገር ክሂል ማስተማሪያነት የቀረቡት ይዘቶች ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲገልጹ የሚያደርጉ መሆን አለመሆናቸውን፣ ይዘቶቹ በተቀናጀ መልክ መቅረባቸውን እንዲሁም ክንውኖች ከትግበራ ቴክኒክ አኳያ መቅረባቸው ተገመግሟል፡፡ ሌሎች ትምህርት ቤቶችን፣ የክፍል ደረጃዎችንና ክሂሎችን ከጊዜና ከገንዘብ ውስንነት አንፃር አያካትትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

## 2.1. የመናገር ክሂል ምንነት

መናገር የሰዉልጅ ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ እምነቱን ወዘተ ለሌላዉ ለመግለፅና ከሌላዉ ጋርም ማህበራዊ ወዳጅነትና ትስስር ለመፍጠር ሲል መረጃዉን የሚያስተላልፍበት የመግባቢ ዘዴ ነዉ፡፡ መናገር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚከናወን የሁለትዮሽ ሂደት ነዉ፡፡ ማቀበያ ክሂል (productive skil) የሆነዉ የመናገር ክሂል ይዳብር ዘንድ መቀበያ ክሂል (Receptive skil) የሆነዉ የማዳመጥ ክሂል መዳበር አለበት፡፡ ይህም ማለት አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ያላቸዉን ትስስር ያሳያል፡፡እንዲሁም ከስንልሳንና ከስነ-ጽሁፍ ጋርም ያለውን ዝምድና ያመለክታል፡፡

ለበርካታ ዘመናት ቋንቋን ማስተማር ቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋት በመተንተን ላይ የሚያተኩር ሲሆን ከክሂሎችም ትኩረት ይሰጣቸው የነበሩት ማንበብና መፃፍ ብቻ ነበሩ፡፡ ይህ አይነት የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን የዘነጋ ነበር (Bailey, 2006.130):: ይህን ችግር ለመቅረፍ በ1970ዎቹ እና በ1980ዎቹ ሰዎች ቋንቋ ሊማሩ የሚችሉት እርስ በርስ በሚያደርጉት መስተጋብር ነው የሚል ሀሳብ ትኩረት እያገኘ መጣ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር መግለጽ ይችሉ ዘንድ በቋንቋ የእርስ በርስ መስተጋብር ማድረግ አለባቸው የሚለው እሳቤ ግንዛቤ ያገኘውና ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ብቅ ያለው በዚህ ወቅት ነው (Bailey,2006.132)::

መናገር በተፈጥሮው የአድማጭን ምላሽ ተራክቦን የሚፈልግ ክሂል ነው፡፡ የአድማጭ ምላሽ መልዕክቱ ምን ያህል እንደተላለፈ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡ (Widdowson, 1984,.58) ንግግር ማቀበያ ክሂል (Active or productive skill) ነው ሲሉ በድሉ (2007፣ 57) ይህን ሀሳብ ሲያጠናክሩ “ማቀበያ ክሂል (productive skill) የሆነው የመናገር ክሂል ይዳብር ዘንድ መቀበያ ክሂል (Receptive skill) የሆነው የማዳመጥ ክሂል መዳበር አለበት” ብለዋል፡፡

ከዚህም ሀሳብ የምንረዳው በሁለቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል ሊኖር የሚችለውን የጠበቀ ትስስር ነው፡፡ ምንም እንኳን ለአንድ ክፍለ ጊዜ የተያዘው የትምህረት ዓላማ አንድ ክሂል ብቻ ቢሆንም በትግበራ ላይ ግን አንዱ ሌላውን ተከትሎ የሚመጣ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ በመሆነም መምህራን የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያቀርቡበት ጊዜ ከማዳመጥ ክሂል ጋር ያለውን ቁርኝት ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡

የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ትኩረት ያላገኙበት ምክንያት ትምህርት ቤቶች አብዛናውን ጊዜ ትኩረት የሚያደርጉት በማንበብና በመፃፍ ክሂሎች ላይ በመሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን በፈተና መመዘን አስቸጋሪ ነው ከሚል እምነት የመነጨ ነው፡፡ ነገር ግን አንድን ቋንቋ በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ ለመገልገል አራቱን ክሂሎች መማር የግድ ስለሚል አስተሳሰቡ ሚዛን እንደማይደፋ (Sesnan, 1997, p.103) ይገልፃሉ፡፡

ማረው(2003፣105) እንደገለፁት የመናገር ክሂል ማድረግን የሚጠይቅ ስለሆነ፣ ድርጊቱ በተለያዩ ስልቶች ይገለፃል፡፡አንደኛው ስልት ቅርፃ ቅርፆችን በመጠቀም የሚደረግ ልምምድ ነው፡፡ተናጋሪ ካለ አድማጭ መኖር አለበት፡፡ በሁለቱ መስተጋብር ቅርፃቅርፆችን ተጠቅሞ የመናገር ክሂልን ማዳበር ይቻላል፡፡ተማሪው በሁለት ቀለማት የተሰራ ግን ከሌሎች ተማሪዎች እይታ የተሰወረ አንድ ቅርፅ ይይዛል፡፡ለተማሪዎች አንድ ባዶ ነጭ ወረቀትና በቀይና በጥቁር ቀለም የሚፅፍ እስኪርብቶ ያድላቸዋል፡፡በመቀጠል ስለቅርፁ ምንነት ገለፃ ወይም ንግግር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም መላምታዊ ሁነቶችም የመናገር ክሂልን ለማለማመድ ያስችላሉ፡፡ለሁሉም ተማሪዎች አንድ አይነት መላምታዊ ሁነት ሊሰጥ ይችላል ወይም እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን ሊመርጥ ይችላል፤ተማሪዎች ምርጫቸውን ወይም አቋማቸውን የሚያጠናክር ንግግር ማድረግ እንዳለባቸው አስቀድመን እንነግራቸዋለን፡፡በዚህ አይነቱ መላምታዊ ሁነት ልምምድ ትክክል ወይም ስህተት የሚባል አይኖርም፡፡

በተጨማሪም ማረው ባስኔትንና ግሩንዲ (1995) ጠቅሰው መላምታዊ ሁነቶች የሚባሉት የሚከተሉትን ይመስላሉ በማለት ገልፀዋል፡፡

- አንድ ሰው በበዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ሰጣችሁ፣ወይም ድንገት ሎተሪ ደረሳችሁ እንበል፤ገንዘቡን ምን ታደርጉታላችሁ?
- ከሁለት የስራ መስኮች በአንዱ ላይ መወሰን አለባችሁ፤አንደኛው በህይዎታችሁ ስትመኙት እና ለመስራት ስትፈልጉት የነበረው ትክክለኛ የስራ መስክ ቢሆንም፣ ደመወዙ ግን ትንሽ ነው፤ሁለተኛው ደግሞ ጥሩ ደመወዝ የሚያስከፍል ቢሆንም፣ የምትፈልግት አይነት ስራ ግን አይደለም-ፍላጎታችሁን የሚነሳሳ አደለም፤ የትኛውን ትመርጠላችሁ?ለምን?
- አንድ ሳይንቲስት ከዚህ በፊት በእናንተ ላይ የደረሰውን ሁሉ እንዳትረሱ የሚያስችላችሁ መድሃኒት አግኝቷል እንበል፤እንዲሁም ከዚህ በፊት በእናንተ ላይ የደረሰውን ሁል እንድትረሱ የሚያደርግ መድሃኒትም አግኝቷል፤ከሁለቱ አንደኛውን መድሃኒት ብቻ መምረጥ አለባችሁ፤የትኛውን ትመርጣላችሁ?ለምን?

  በአጠቃላይ እነዚህንና ሌሎችንም መሰል አጋጣሚዎችን በመፍጠርና በማመቻቸት ተማሪዎችን በተናጠል ወይም በቡድን የመናገር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማለማመድ ይቻላል፡፡

“የመናገር ክሂል አፍልቆታዊ በመሆኑ ሃሳባችንን፣ ስሜታችንን እና ምኞታችንን የምንገልጽበት፣ ችግሮቻችንን የምንፈታበት እና ማህበራዊ ህይወት የምንመሰርትበት በአጠቃላይ ተግባቦታዊ ተግባራትን የምናከናውንበት አይነተኛ መሣሪያ ነው” በማለት (McDonough and Shaw1993:153) ይገልፃሉ፡፡ ቃላዊ ተግባቦት የሚካሄደው በተናጋሪውና በአድማጩ መካከል ባለው መስተጋብር ሲሆን የአፍላቂ እና የተቀባይ ክሂልን ግንዛቤና ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ ይጠይቃል፡፡ ይህን ሃሳብ በመደገፍ (Nunan,1989:27) “የቃል ተግባቦት ባህሪ መስተጋብራዊ ተግባርን ተጠቅመው ተማሪዎች የራሳቸውን ባህል፣ ልምድና እውቀት መሠረት በማድረግ የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲፈጥሩና ማህበራዊ ግንኙታቸውን እንዲያጠናክሩ በተጨማሪም አንድን መረጃ ወደተፈለገው ሌላ አካል ለማስተላለፍ ያግዛቸዋል” በማለት ይገልፃሉ፡፡

## 2.2 የመናገር ክሂልን የማስተማር ዓላማ

የመናገር ክሂልን የማስተማር ዓላማ ተማሪዎችን ጥሩ ተናጋሪ ለማድረግ ነው፡፡ (Byrne, 1987:8) እንደሚሉት መምህሩ ውስን ወይም ነፃ ንግግርን ጐን ለጐን በማስኬድ

የተማሪዎችን ችሎታ ከፍ ማድረግ ሲሆንበተጨማሪም የመናገር ክሂል የሚከተሉት የማስተማር ንዑስ አላማዎች እንዳሉት ይገልፃሉ፡፡ እነሱም፡-

- የቋንቋውን ድምፀ ልሳናዊ ባህሪያት አድማጭ ሊረዳ በሚችልበት መንገድ መጠቀም እንዲችሉ፣
- መስተጋብራዊ በሆነ የተግባቦት ሂደቶች መሳተፍ እንዲችሉ፣
- በንግግር ሂደት ሃሳብን በቅደም ተከተል አዋቅረው ማቅረብ እንዲችሉ፣
- መረጃን መስጠት፣ ማዝናናትና ማሳመን እንዲችሉ ማድረግ ነው ይላሉ፡፡

ከገለፃው መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ የቋንቋ መምህር ክፍል ውስጥ ገብቶ ተማሪዎችን ከማስተማሩ በፊት ቅድሚያ ማሰብ ያለበት ይህን ክሂል ማስተማሩ ወይም ማለማመዱ አላማው ምንድነው? ከዚህ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች ምን ይጠበቃል? የሚለውን ሃሳብ ቅድሚያ ማሰላሰል ይገባዋል ማለት ነው፡፡

Scrivener (1994:59) አገላለጽ "በቋንቋ ክፍል ውስጥ ለሚደረገው ንግግር በርካታ ተግባራት ቢኖሩትም ዋናው አላማ ለንግግር የልምምድ እድል መስጠት ነው፡፡ ትኩረት የሚሰጠውም ከትክክለኛነት ይልቅ የቋንቋ ፍሰትን ለማሻሻልና ተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት በማሳደግ ሃሳባቸውን በትክክልና በተገቢው መንገድ መግለጽ እንዲችሉ እድል መፈጠር ነው" ይላሉ፡፡

እንዲሁም Murcia (1991:337) አገላለፅ በቃለ ንባብ፣ ሚናነጠቃልዩ ልዩ ትምህርታዊ ውይይቶች ድራማና ተውኔቶች በሥነ ጽሁፍ ዙሪያ በሚያጠነጥኑ ነገሮች ተጠቅመው ተማሪዎች ተገቢ ወደሆነው ተግባቦታዊ ንግግር መግባት እንዲችሉና የቋንቋ አውቀትና ማህበራዊ አውድን የመገንዘብ ብቃት እንደያገኙ መንገድ ለማመቻቸት ያስችላል፡፡

ከላይ የተገለፁት ሃሳብ ባጭሩ ሲቀመጡ የመናገር ክሂልን የምናስተምርበት ዓላማ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ሲሆን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚያከናውኗቸው ተግባራት አማካይነት ትክክለኛነትንና የቋንቋ ፍሰትን በሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ ነው፡፡ ትክክለኛነትን ለማምጣት የቋንቋውን ህግ ወይም የሥነ ድምጽ፣ የቃላት፣ የሰዋሰው አወቃቀር ጠንቅቆ በማወቅ ሙሉ ስሜት መስጠት

የሚችል አሳክቶ ማፍለቅን የሚጠይቅ ሲሆን የቋንቋውን ስርዓት ብቃትን ለማምጣት ደግሞ ማህበራዊ አውድን፣ የቋንቋውን ተግባቦታዊ ብልሀቶችን በመጠቀም ተቀባይነት ባለው መንገድ ንግግርን እያቀናበሩ ያለእንከን እንዲያወጡ ለማድረግ ያላሰለሰ ልምምድ ማድረግ ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡

## 2.3. የቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች

የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች የሚባሉት መረሃ ትምህርት የመምህሩ መምሪያና የተማሪዉ መማሪያ መፃህፍት ናቸዉ፡፡ እያንዳንዳቸዉ እንደሚከተለዉ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

ሀ. መርሃ ትምህርት፡- መርሃ ትምህርት ከስርዓተ ትምህርት ጠበብ ያለ፣ የትምህርቱን አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችን በግልፅ የሚያሳይ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጠቁሙ፣ የምዘና ዘዴዎቹንና መረጃ መሳሪያዎችን የሚያሳይ ሰነድ ነዉ(cunning worth,1984,22) እንዲሁም (widdson, 1990,129) የቋንቋ መርሃ ትምህርት ለመምህራን እንደመመሪያ ሆኖ እንደሚያገለግላቸዉ የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን በማሳየት የመማር ማስተማር ሂደትን እንዴት እንደሚተገብሩና ማስተማር ክንዉኖችን እንዲያጎለብቱ የሚጠቁም መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳዉ መርሃ-ትምህርት ማለት ከስርዓተ ትምህርት ጠበብ ያለ ሆኖ ስርዓተ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የሚዋቀር፣ የትምህርቱን አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችን በግልፅ የሚያሳይ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጠቁም፣ የምዘና ዘዴዎችንና መረጃ መሳሪያዎችን ዝርዝር የያዙ ሰነድ መሆኑን ነዉ፡፡

ለ. የመምህሩ መምሪያና የተማሪዉ መማሪያ መፅሐፍ

Harmer(1991,257) እና Richard and Rodgers(1986,25)እንደገለፁት የቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፎች የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚመሩ፣ የትምህርቱን መነሻና መድረሻ የሚጠቁሙየተለያዩ ይዘቶችን በምሳሌ አስደግፈዉ የሚያቀርቡ መልመጃዎችንና የተለያዩ ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎች እንዲለማመዱ የማድረጉ መሆናቸዉን አስረድተዋል ፡፡

ከላይ ከተገለፁት ከምሁራኑ ሀሳብ መገንዘብ የሚቻለዉ የመምህሩ የተማሪዉን መማሪያ መፅሐፍ እንዴት ማስተማር እንዳለበት አቅጣጫ የሚያመለክት ነዉ፡፡

የተማሪዉ መማሪያ መፅሐፍ ደግሞ ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዲከታተሉ የሚረዳና የተለያዩ ተግባራትን እነዲሰሩ የሚያስችል የማስተማሪ መሳሪያ መሆኑን ነዉ፡፡

## 2.4. የመናገር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት

Harmer (1991:15) መናገር ክሂልን ትምህርት አስፈላጊነት ሲገልፁ "የመናገር ክሂል ከጽሁፍ በበለጠ መልኩ ሃሳብን ለመግለጽ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማብራራት ወዘተ የምንጠቀምበት ክሂል ሲሆን ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው ሃሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ ዘመናዊ በሆነ የክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ዘዴ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም ሰፊ ቦታ የሚሰጠው በመሆኑ በተገቢው መንገድና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ማስተማር ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም በድሉ (2007፣87) "የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ መማሩ አስፈላጊነት ተማሪዎች መልዕክትን በምክንያትና ውጤት አቀናጅቶ የማቅረብና የቋንቋውን ስርዓት ያለመጠበቅ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል፤ በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በክፍል ውስጥ ማስተማር ተማሪዎች ጥሩ የመናገር ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡" በማለት ገልፀዋል፡፡እንዲሁም Harmer (2007 :16) የመናገር ክሂል ትምህርት ለተማሪዎች ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ይኸውም፡ -

- ተግባቦታዊ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ፣
- ከሰዎች ጋር ለመወያየትና ለመደራደር እንዲችሉ፣
- የቃል ሪፖርት እንዲያደርጉ፣
- የሌላ ሰው ድጋፍና ምክር ለማግኘት እንዲጠየቁ፣
- አስተያየቶችን በመረጃ አስደግፈው ማቅረብ እንዲችሉ፣
- ከኢመደበኛ የአነጋገር ስልት ይልቅ ወደ መደበኛ የአነጋገር ስልት እንዲጠጉ፣
- ሃሳብን በተጠያቃዊ ቅደም ተከተል ማቅረብ እንዲለማመዱ ለማድረግ ወዘተ አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑን ምሁራኑ ይገልፃሉ፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች ተፈጥሯዊ የሆነውን የንግግር ችሎታ እንዲያዳብሩ በክፍል ውስጥ ጊዜና ዘዴ ተመቻችቶለት በክፍል ውስጥ ትምህርቱ መሰጠቱ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.5. ተግባቦታዊ አቀራረብ የመናገር ክሂልን ለማስተማር ያለው ድርሻ

በተግባቦታዊ አቀራረብ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ አብዛኛው ጊዜ አገልግሎታዊም ሆነ ሥነ ልቦናዊ አላማው ከተማሪው ፍላጐትና ችሎታ ጋር የተመጣጠኑ የተለያዩ ተግባራት ይቀርባሉ፡፡ በቡድን ወይም በጥንድ በመሆን እርስ በራሳቸው ሃሳብ ለሃሳብ እንዲለዋወጡ፣ ሌሎች የሚያስተላልፉትን ሃሳብ መረዳት እንዲችሉ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ እና በተናጋሪውና በአድማጭ መካከል የመረጃ ልውውጥ እንዲያካሂዱ አስተዋጽኦ ያደርጋል (Riachards, and Rodgers, 1986:71) በማለት ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም ምሁሩ ተግባቦታዊ አቀራረብ የመናገር ክሂልን ለማዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ሲገልፁ፡-

- በክርክር፣ በውይይት ጊዜ ከሰዎች ጋር ሃሳብ ለሀሳብ የመለዋወጥን፣
- አዳምጠው ወይም አንብበው  ያገኙትን መረጃ ማብራራትን፣
- ጥሩ አድማጭ በመሆን ጥሩ ተናጋሪ መሆንን፣
- ከሰዎች ጋር ሃሳብ ለሀሳብ መለዋወጥን  ያካትታል፡፡

Fairclough (2006) እንደሚገልፁት የተግባቦት ትንተና መሠረት ከሚያደርጋቸው ጉዳዮች አንዱ ተናጋሪ ሲናገር አድማጩ፣ የተደረገውን ነገር መሠረት አድርጐ ምላሽ ሲሰጥ የሚታየውን ክንውን መተንተን ነው፡፡ ምላሹም አወንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል ዋናው ቁም ነገር ግን ንግግር መካሄዱ ነው፡፡ በተጨማሪም አለም(1987፣ 42)በተግባቦታዊ ማስተማሪያ ዘዴ የሚያስተምር መምህር በክፍሉ ውስጥ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም የግድ ይለዋል ፡፡ ከስልቶቹም ውስጥ ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አንድ ውይይት ወይም ክርክር ለማድረግ የሚያስችል ሁነት ማዘጋጀት፣ምን አይነት ንግግር ለምን አይነት አላማ በምን አይነት አውድ ውስጥ እንደሚነገር መንገር እና ተማሪውን ማነሳሳት፤
- እንደአስፈላጊነቱ በግል ፣ በጥንድ ወይም በቡድን እንዲናገሩ መፍቀድ፤
- በእንቅስቃሴ ፣በስእል ወይም በጎላ መንገድ  ትምህርቱን ለማብራራት የሚያገለግሉ ደጋፊ ስልቶችን መጠቀም፤
- መምህሩ  አስቀድሞ ባወጣው ወይም ባስቀመጠው  መመዘኛዎች አንጻር ተማሪዎቹ ባደረጉት ንግግር እንዲገመገሙ ማድረግ እና በመጨረሻም

መምህሩ ማረም እና ይህን ተግባር የሚፈለገው ለውጥ እስኪገኝ ድረስ ደጋግሞ ማሰራትዋናዋናዎቹ ተግባራት ናቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡

## 2.6. የመናገር ክሂልን ለማስተማር የስነ-ፅሑፍ ሚና

እንደ በድሉ (2007፣18) አገላለፅ የስነ-ፅሑፍ በትምህርት ዉስጥ መካተት ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የማንበብን፣ በመካከለኛ ደረጃ ደግሞ የማዳመጥን፣ መናገርና የመፃፍን ክሂሎች እንዲያዳብሩ ያግዛል፡፡መምህሩ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲያነብ ተማሪዉ ያዳምጣል፡፡ የተነበበዉን አስመልክቶ የሚደረገዉ የተማሪዎች ዉይይትም ደማቅ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የስነ-ፅሑፍ ስራን አስመልክቶ በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ዉይይት ተማሪዎችን ስለሚስብ የተሳታፊነታቸዉን ደረጃ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ተማሪዎች ድራማዎችን ሲሰሩ፣ ግጥሞችንና አጫጭር ሲያነቡ የመናገርና የማንበብ ክሂላቸዉ ይዳብራል በማለት አብራርተዋል፡፡

የስነ-ፅሑፍ ስራዎች ደራሲዉ ከአዕምሮዉ በመጭመቅ ኪናዊ በሆነ መንገድ እዉነትንና ዉበትን አቀናጅቶ የሚያቀርባቸዉ በመሆናቸዉ ተማሪዎችን የመሳብ፣ የማጓጓትና ስሜት የመቀስቀስ ኃይላቸዉ ከፍተኛ ነዉ(Lazar,1993,15)እንደምሁሯ አገላለፅ በተለያዩ ልቦለዶች ዉስጥ ያሉ ምልልሶች፣ ዉይይቶች፣ ታሪኮች፣ የመሳሰሉትን የስነ-ፅሑፍ ስራዎች የተማሪዎችን ቀልብ የመግዛት ኃይላቸዉ ከፍተኛ በመሆኑ የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በሰፊዉ ከማሳደጋቸዉም በላይ ስሜታቸዉን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀስቀስ የአብዛኛቸዉን ተማሪ ተሳትፎ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም Murcia(1991,337)በስነ-ፅሑፍ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ነገሮች ማለትም ሚና ጨዋታ፣ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ዉይይቶችንና ተዉኔቶችን ተጠቅመዉ ተገቢ ወደሆነዉ ተግባቦታዊ ንግግር መግባት እንዲችሉ፣ የቋንቋ እዉቀትንና ማህበራዊ አዉድን የመገንዘብ ብቃት እንዲያገኙ ማመቻቸት እንደሚቻል ይገልፃል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለፁት የተለያዩ የምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለዉ ተማሪዎች የስነ-ፅሑፍ ስራዎችን ተጠቅመዉ የታያቸዉን ወይም በአዕምሯቸዉ የቀረጧቸዉን እና የተሰማቸዉን ስሜት የሚገልፁበትን ሁኔታ በተለያዩ መንገድ መግለፅ ይችላሉ ማለት ነዉ፡፡

## 2.7. የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የመምህራን ተግባራት

መምህራን የተማሪዎቻቸው የመናገር ክሂል እንዲዳብርና የንግግር ትምህርት ፍላጐት እንዲያድርባቸው ማበረታታትና ተከታታይ ልምምድ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡ (Nunan,1991:2) እንደገለፁት አብዛኞቹ የቋንቋ መምህራን አላማ ትክክለኛውን የማስተማሪያ ዘዴ በመምረጥ በተግባር ላይ ማዋል ነው፡ ፡ በተጨማሪም (Sahar, 2014:4) በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርቱን ሲተገበሩ የመምህራን ተግባራት የሚከተሉት እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

- ✓ ተማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው ለችግሮች መፍትሄ የሚሆኑ ሃሳቦችን እንዲፈልጉ ማድረግ፣
- ✓ የአመቻችነት ተግባር መጫወት፣
- ✓ ተማሪዎች እርስ በርስ መስተጋብር እንዲፈጥሩ ማበረታታት፣
- ✓ የመማሪያ ክፍሉን ሁኔታ ለሚያስተምረው የንግግር ይዘት ምቹ እንዲሆን ማድረግ እና የተማሪዎች በራስ የመተማመን ሁኔታ እንዲዳብር ያመቻቻል፡፡

ስለዚህም መምህሩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ቀጥተኛ ተዋናይ ሆኖ ሳይሆን አንዳንድ የቡድን አባል ራሱን በመቁጠር ተማሪዎች በሚሰሩበት ወቅት ተሳታፊ በመሆን ተማሪዎችን ይከታተላል፡፡ በዚህ ወቅት ተማሪዎች ከርዕሰ ጉዳዩ እንዳይወጡና ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የማይሄድ ነገር እንዳያመጡ አቅጣጫን ያመለክታል፡፡ ተማሪዎች ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ፣ ሃሳብ እንዲያጋሩ፣ በቡድኑ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉና ለችግሮቻቸው መፍትሄ የሆኑ ሃሳቦችን እንዲያመጡ ማበረታታት የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚቀጥልበትን ሁኔታ የሚያመቻች መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡
ማረው (2003፣108)"ከዚህ በፊት በሚያውቁት ገጠመኝ ላይ በመነሳት ተማሪዎች የሚናገሩባቸውን ሁኔታዎች መምህራን ማመቻቸት አለባቸው፤በዚህም የተማሪዎቹን የመናገር ችሎታ ለማዳበር፡-

- በጉዳዩ ላይ በሚደረገው ውይይት ሁሉም ተማሪዎች ከአንድ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ አለማድረግ፣

- ተማሪዎች ስለ ዓለም ስለህይዎት አዲስ አመለካከታቸውን እንዲገልፁ ማደፋፈር፣
- ተማሪዎች እንዲጠይቁና የራሳቸውን አመለካከት ወይም ፍርድ እንዲሰጡ እድል መስጠት ያስፈልጋል በማለት ገልፀዋል፡፡

## 2.8. የመናገር ክሂልን በመማር ሂደት የተማሪዎች ተግባር

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ዋነኛ ተሳታፊና ተዋናኝ መሆን አለባቸዉ፡፡ ስለሆነም ከፍተኛ ሚና አላቸዉ፡፡"በተለይ የመናገር ክሂልን ለማዳበር ፍለጎት ያለዉ ተማሪ የራሱን ሃሳብ ለሌላወገን ለማስተላለፍ መሞከር እና የሌላዉንም ሃሳብ አዳምጦ የመረዳት ሃላፊነት አለበት፡፡ በሚማረዉ ቋንቋ ብቃት በይኖረዉም ብቃቱን ለማሻሻል ሰፊ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታል" (Freeman and Long, 1991,p.199):: ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለዉ አንድ ተማሪ ንግግርን በሚማርበት ጊዜ በቋንቋዉ የመናገር ብቃት እስከሚኖረዉ ድረስ ችላሳይል እና ሳይሰለች መማር ወይም መለማመድ እንዳለበት ነዉ፡፡ እንዲሁም Richards and Rodgers(1986,)በቋንቋ ትምህርት ንግግርን የሚያስተምር መምህር በሚሰጠዉ የመወያያ፣ የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎች በየቡድናቸዉ ሃሳብ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ እያንዳንዱ ተማሪ የመናገር እድል ስለሚያገኝ የመናገር ችሎታዉ እየተሻሻለ ይሄዳል በማለት ይገልፃሉ፡፡

## 2.9. የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት

እንደ Harmer ,(2007:129)፣ አገላለጽ የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ የተለያዩ የማስተማሪያ ተግባራትን በመጠቀም ሲያከናውኑ በይዘቱ እና በክንውኑ ላይ ያተኮሩ ተግባራት አሉ፡፡ እነዚህ ተግባራትን ንግግርን ለማስተማር በውይይት፣ በክርክር እና በጭውውት መልክ የሚከወኑ ሲሆን ተማሪዎቹ ለሚመጥናቸው ደረጃ የመለማመጃ ክንውኖች መምረጥ ተገቢ ነው፡፡ የመናገር ክሂልንለማስተማር የሚከናወኑ ተግባራት የሚከተሉት እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

2.9.1 **ስዕሎችን በንግግር መግለጽ፡-**በዚህ ተግባር ለማስተማር ተማሪዎችን በቅድሚያ በቡድን መከፋፈል፡፡ በጥንድና በቡድን ተከፋፍለው ለተቀመጡት ተማሪዎች የተለያዩ ስዕሎችን በመስጠትና በተወሰኑ ደቂቃዎች የተሰጣቸውን

ስዕል የሚገልፁ ሃሳቦችን መፃፍ ከዚያም በክፍል ውስጥ ለሚገኙት ተማሪዎች ሐሳባቸውን በንግግር እንዲገልፁ በማድረግ ይከናወናል፡፡

2.9.2. **ልዩነትን በንግግር መግለጽ፡-**ይህ ተግባር ተማሪዎችን በቢጤ በመመደብና የተለያዩ ስዕሎችን ፎቶ ግራፎችን የአንድን ነገር ቅርጽ፣ መጠን፣ ርዝመት፣ ወዘተ የሚገልፁ ነገሮችን በመስጠት የሚለዩባቸውን ባህሪያት በንግግር እንዲያቀርቡ የሚለማመዱበት ነው፡፡ በጋራ ሆነው የተሰጧቸውን ነገሮች ልዩነት ላይ ሲወያዩ የሚያነሷቸው ጥያቄዎችና የሚሰጧቸው ምላሾች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ያደርጋቸዋል፤ የመናገር ክሂላቸውም ይሻሻልላቸዋል፡፡

2.9.3. **ተመሳሳይነትን በንግግር መግለጽ፡-**ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ በማደራጀት በጋራ የያዟቸውን ነገሮች የጋራ የሆኑ ተፈጥሯዊ ባህሪያቸውን በንግግር በመግለጽ ክሂሉን የሚለማመዱበት ስልት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መምህሩ መመሪያ ከመስጠት ውጪ ጣልቃ በመግባት ማብራሪያ ሊሰጣቸው አይገባም፡፡

2.9.4 **ችግርን የመፍታት ተግባራት፡-**ይህ ጊዜ ተማሪዎች አንድን ችግር በቡድን እንዲፈቱ የሚያደርግ ሲሆን ከመምህር ገለፃ ነፃ የሆነ ራሳቸው የሚሳተፉበት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መምህሩ እንደ አመቻች፣ ተቆጣጣሪና አቅጣጫ ጠቋሚ ሆኖ የሚመራበት የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ሀላፊነት ላይ ያለውን ሰው በመወከል ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት፣ የምክር አገልግሎትን ለመስጠት፣ ውሣኔ ለመስጠትና ለመሳሰሉት ጉዳዮች በቋንቋው ተጠቅመው ንግግርን የሚለማመድበት ዘዴ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ የመለማመጃ ተግባር ከተማሪዎቹ የልምድ ደረጃ ጋር ተገናዝቦ የሚቀርብ ነው፡፡ እንዲሁምልምምዱ ከመናገር ክሂል በተጨማሪ ማህበራዊ ችግሮችን ከራሳቸው ጉዳይ ጋር እያይዘው መፍትሂ የመሻት ልምምድን ያዳብርላቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡

2.9.5. **ታሪክ መናገር፡-** ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ለእያንዳንዳቸው ቡድን ተከታታይነት ያላቸው መልዕክት የያዙ ስዕሎች ይሰጣሉ፡፡ የቡድኑ አባላት ስዕሎቹን ከተመለከቷቸው በኋላ ይሰበሰባሉ፡፡ ከዚያም ከእያንዳንዱ ቡድኖች አንዳንድ አባል በመውሰድ አዳዲስ ቡድኖች ይመሰርታሉ፡፡ አዳዲሶቹ ቡድኖችም ቀደም ሲል ያዩትን ስዕላዊ መግለጫ ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ይነጋገራሉ በመቀጠል እያንዳንዱ ቡድን ያቀርባል፡፡

ያቀረቡት ታሪክ ተመሳሳይ ሃሳብ መያዝ አለመያዙን ለማረጋገጥ የየራሳቸውን ታሪክ ለክፍሉ ተማሪዎች ያቀርባሉ በማለት (Harmer 2007:130) ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም Sesnan (1997:16) እና Fayzeh (2012) ልጆች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ታሪክ እንዲናገሩ ማበረታታት አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው የሚከተሉት አይነት ታሪኮችን እንደናገሩ ማድረግ ጠቃሚነት እንዳለው ጠቁመዋል፡፡ እነሱም ከዚህ በፊት የሰሟቸውን ታሪኮች ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ፣ የራሳቸውን ታሪኮች ፈጥረው እንዲናገሩ ማበረታታና እና ስላዩአቸው ወይም ስላከናወኗቸው ነገሮች ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲናገሩ እድል መስጠት የመናገር ክሂላቸውን ለማሳደግ ይረዳል፡፡

2.9.6 **ሚና ጨዋታ፡-** Harmer (2007:130) እናFayzeh (2012) እንደሚያስረዱት ተማሪዎች በተለያዩ ማህበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው የተለያዩ ማህበራዊ ሚናዎች አሏቸው፡፡ ለምሳሌ አቅጣጫን መጠቆም፣ ከሱቅ መገዛዛትና መሸጥ የመሳሰሉት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ላሉ ተማሪዎች በጣም ጠቃሚ ተግባራት ናቸው፡፡

እንዲሁም በድሉ (1996፡94-95) መናገርን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት ብለው ከጠቀሷቸው ውስጥ፡-

**ሀ. ጭውውት**፡- ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው እና ዳራዊ እውቀታቸው አግባብነት የተመረጡ ቅንጫቢዎችን በመጠቀም የሚያካሂዱት የጭውውት ተግባር እውነተኛ አውድን ይፈጥራል፡፡ እንዲሁም በዚህ ሃሳብ ላይ (Sesnan 1997:16) ጨዋታዎችን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ሲታሰብ የተማሪዎችን የእድሜ፣የባህል፣የእውቀትልዩነት በመረዳት ችግሩን መፍታት ይጠበቅበታል በማለት የበደሉን ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡

**ለ. ቃላዊ ሪፖርት**፡- ይህ ዘዴ ተማሪዎች ያነበቡትንና ያዳመጡትን ጉዳይ በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለጽ ችሎታ በንግግር ችሎታ በመናገር የሚያቀርቡበት ነው፡፡ ተማሪዎች ቃላዊ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ጊዜ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር መምህራን የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**ሐ. ቃለ መጠይቅ፡-** ይህ የማስተማሪያ ብልሀት ተማሪዎች አንድን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክተው በቃለ መጠይቅ ከሰዎች መረጃ የሚሰበሰቡበትና ያገኙትን መረጃ አቀናብረው በክፍል ውስጥ በንግግር የሚያቀርቡበት ነው፡፡ ይህን ሃሳብ በማጠናከር (Fayzeh 2012) ቃለ መጠይቅ በሚያዘጋጁበት ጊዜ መምህሩ የጥያቄዎቹን ብዛትና ጥራት መመልከት ይጠበቅበታል፡፡ በክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከክፍል ውጭም ልምምድ እንዲያደርጉ ማበረታታት ይጠበቅበታል በማለት ይገልፃሉ፡፡

**መ. ጥያቄ መጠየቅ፡-** አብዛኛውን ጊዜ በቋንቋ ክፍል ንግግርም ሆነ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ተግባር ነው፡፡ መምህራን ንግግርን በዚህ ስልት ሲያስተምሩ ማድረግ ያለባቸው ተግባራት አሉ፡፡ ከእነሱም ውስጥ ስለንግግሩ ተግባር የተማሪዎችን ትኩረት መሳብ የሚችል መግቢያ ወይም ፍንጭ መስጠት፣ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በራሳቸው መንገድ እንዲገልፁ ማበረታታት፣ መምህራን የራሳቸው ስሜት የሚያንፀባርቁ ርዕሰ ጉዳዮችን ከመምረጥ ይልቅ ተማሪዎች በሚመርጧቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ መፍቀድ ወዘተ ናቸው በማለት አስቀምጠዋቸዋል፡፡

## 2.10. ንግግርን የማስተማር ሂደት

ንግግር የተለያዩ ንዑሳን ተግባራትን የያዘ ሂደት እንጅ በአንድ ዉስን ጊዜ የሚከናወን ነጠላ ተግባር አይደለም፡፡ ንግግሩ ተመቅረቡ በፊት እና ከቀረበ በኋላ ሊተኮርባቸዉ ሊገቡ ተግባራት አሉ በማለት (በድሉ 2007፣ 92 — 93) በመግለፅ እነዚህን ተግባራት የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

### 2.10.1. የቅድመ ንግግር ተግባራት

ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ በንግግር ተግባር ከመሳተፋቸዉ በፊት ቀድመዉ ሊያከናውኗቸዉ ተግባራት ናቸዉ፡፡ እነሱም፡-

- ✓ ንግግር የሚደረግበትን ርዕስ መምረጥ፣
- ✓ በተመረጠዉ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ፣
- ✓ ንግግር የሚደረግበትን ዓላማ ማወቅ፣
- ✓ አድማጭን መወሰን እና ዋናዋና ነጥቦችን በማስታወሻ መያዝ ናቸዉ፡፡

### 2.10.2. የንግግር ተግባራት

ተማሪዎች የቅድመ ንግግር ተግባራትን ካጠናቀቁ በኋላ ንግግር ያቀርባሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ትኩረት ሊያደርጉባቸዉ የሚገቡ ተግባራት፡-

- ✓ ርዕሱን ለአድማጭ ማስተዋወቅ፣
- ✓ የንግግሩን አላማ ማስተዋወቅ፣
- ✓ አድማጭን በዓይን መቅኘት፣
- ✓ በንግግሩ መጨረሻ ምስጋና ማቅረብ ናቸዉ፡፡

### 2.10.3. የድህረ ንግግር ተግባራት

ተናጋሪዎች አድማጮቻቸዉን ምን ያህል መልዕክቱን እንደተረዱ የሚገመግሙበት ነዉ፡፡ ይህም ሂደት የተወሰኑ አድማጮችን በዘፈቀደ በመምረጥ ስለንግግሩ መረጃ እንዲሰጡ ጥያቄ መጠየቅ ነዉ፡፡

## 2.11. የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ደረጃዎች

የመናገርን ክሂል ትምህርት ለማስተማር ዝግጅት እንደተደረገዉ ሁሉ አቀራረቡም ከፍተኛ ጥንቃቄን ተሚጠይቅ ነዉ፡፡ ስለዚህ መናገርን የማስተማር አላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተለዉን የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ደረጃዎች መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡

### 2.11.1. አቀራረብ (traditional present)

እንደ (Kember.2009) አገላለፅ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍላቸዉ ዉስጥ ቁጭ ብለዉ ከመምህሩ የሚተላለፍላቸዉን እዉቀትና መረጃ የሚወስዱበትና የሚቀስሙበት ነዉ፡፡ ይህ ማለት የመምህሩ ተግባር እንደመረጃ አቀባይ መሆን ነዉ፡፡ መምህሩ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚቀርበዉን ተግባር በግልፅና በማይረሳ መልኩ ማቅረብ አለበት፡፡ በዚህ ደረጃ የመናገር ክሂል ትምህርት በምልልስ መልክ ወይም በንባብ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በምልልስ መልክ የሚቀርበዉ ርዕሰ ጉዳይ፡-

- ✓ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ሊያሳድግ የሚችል፣

- ✓ በእዉኑ ዓለም ላይ ሊደረግ የሚችል የገሃዱ ዓለም ሰዎች ሊያደርጉት የሚችሉትና ክክፍል ደረጃዉ ጋር ተመጣጣኝነት ያለዉ የንግግር ተግባር፣
- ✓ ምልልሱ ተማሪዎችን ወደ ልምምድ ተግባር ሊመራ የሚችል መሆን አለበት፡፡

እንዲሁም በንባብ መልክ ሲቀርብ፡-

- ✓ ርእሱን ማስተዋወቅ፣
- ✓ ስለርእሱ ያላቸዉን የቀደመ እዉቀት መሰረት በማድረግ እንዲናገሩ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

### . 2.11.2. ልምምድ (practice )

በልምምድ ወቅት አብዛኛዉን ተግባራት የሚያከናዉኑት ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ Byrne (1987,34) እንደሚገልፁት ይህ ደረጃ አስቀድሞ በቀረበዉ የትምህርት አቀራረብ መሰረት በቋንቋዉ የመጠቀም ችሎታቸዉን ለማዳበር የሚለማመዱበት ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፡-

- ✓ ገምተዉ እንዲናገሩ የሚያስችሉ መልመጃዎች ለምሳሌ በቀረበላቸዉ ስዕል ላይ ሊኖር የሚችለዉን የተመለከቱትን እንዲገምቱ ማድረግ፣ እንዲሁም ተማሪዎች በጣም የሚወዱትን ቀለም፣ የስፖርት አይነት፣ ወዘተ እንዲገልፁ ማድረግ፣
- ✓ የባለፈዉን ሳምንት የመጨረሻ ቀን ወይም ምሽት የሰሩትን ስራ እንዲጠያየቁ ማድረግ፣
- ✓ ክፍት ጥያቄዎችን በመስጠት ሃሳባቸዉን በተለያየ መንገድ እንዲገልፁ ማድረግና የመሳሰት ሊጠቀሱ የሚችሉ መነሻዎች ናቸዉ፡፡

### 2.11.3. አፍልቆት (produce)

ይህ ደረጃ ከመምህሩ ትዕዛዝ ነፃ ሆነዉ ቋንቋዉን እነደፈለጉት የሚጠቀሙበት፣ ሃሳባቸዉን በንግግር ለመግለፅ የሚጥሩበት ነዉ፡፡ እንደ (Harmer.1991) አገላለፅ መምህሩ ተማሪዎች ሃሳባቸዉን በነፃነት እንዲገልፁ የሚረዱ ተግባራትን በመስጠት የመምራትና የማማካር ሚናን መጫወት ይኖርበታል፡፡ በአፍልቆት ደረጃ ዋናዉ ትኩረት ተማሪዎች በቀላሉ እና በነፃነት የሚግባቡበትን አዉድ መፍጠር እንዲሁም በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነዉ፡፡

በተጨማሪም መምህሩ ተማሪዎች የራሳቸዉን የቋንቋ ዕዉቀት ተጠቅመዉ ሃሳባቸዉን የሚገልፁበት እድል ማመቻቸት የጠበቅበታል፡፡ ይህን ተግባር እዉን ለማድረግ የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን ማለትም ዉይይቶችን፣ ክርክሮችንና ሌሎች ተግባራትን በማደራጀት እንዲናገሩ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

### 2.11.4. ምጋቤ ምላሽ(feed back)

እንደ Gower *et. al.* (1995, 163) አገላለፅ በመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ምጋቤ ምላሽ መስጠት በጣም ጠቃሚ ከሆኑት የመምህራን ተግባራት ዉስጥ አንዱ ነዉ፡፡ ቀጣይነት ያለዉ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የተማሪዎችን ስኬትና ለዉጥ ለመገምገም ይረዳል፡፡ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ የተለያዩ መንገዶችን የሚከተል ሲሆን ምስጋናና ማበረታቻ እንዲሁም እርማት መስጠት ተጠቃሽ ናቸዉ ይላሉ፡፡ እንዲሁም "የቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ከድክመት ይልቅ ጥንካሬን መነሻ በማድረግ መስጠት በእርማት አሰጣጥ ደግሞ ለተማሪዉ ለራሱ ቅድሚያ በመስጠት ስህተቱን እንዲናገር የሚደረግበት ሲሆን ተማሪዉ ካልተረዳዉ ሌሎች የክፍል ጓደኞቹና መምህሩ ስህተቱን የሚጠቁሙበት ሂደት ነዉ" (FaYzeh,2012.p,6) በማለት ይገልፃሉ፡፡

## 2.12. የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች

በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት በሚከናወንበት ወቅት ተግባሩን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች በመምህሩም ሆነ በተማሪው ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ይኖራሉ፡፡ በመምህሩ በኩል የማስተማር ችሎታ፣ የብቃት ማነስ፣ የዝግጅት ማነስ፣ የክፍል አመራር ችሎታ ማጣት ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተማሪዎች በኩል ደግሞ መታቀብ፣ የሚናገሩትን ማጣት፣ ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያማከለ ተሳትፎ አለመኖር እንደሆኑ (በድሉ2007፣ 88-89) በመግለጽ ከተዘረዘሩት ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ሀ. መታቀብ**፡- የሚናገር ሰው ከሚያዳምጥ፣ ከሚያነብ ወይም ከሚጽፍ ሰው የበለጠ የሌሎችን ትኩረት ይስባል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ እንሳሳታለን በሚል አመለካከት ፍርሃት ስለሚያድርባቸው ከመናገር

ይልቅ ዝምታን ይመርጣሉ፡፡ እንዲሁም “የምናገረው ነገር ለሌሎች ተደማጭና ሳቢ ሊሆን አይችልም” በሚል እምነት ሃሳባቸውን በውስጣቸው አምቀው ስለሚይዙ ለንግግር በሚዘጋጁ ተግባራት በፈቃደኝነት አይሳተፉም፡፡

**ለ. የሚናገሩትን ነገር ማጣት፡-** ተማሪዎች የመናገር ፍላጐት እያላቸው አንዳንድ ጊዜ ለንግግር ስለተመረጠው ጉዳይ በቂ መረጃ ስለማይኖራቸው ለመናገር አይደፍሩም፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ለመናገር የተመረጠው ርዕስ የተማሪዎችን ደረጃ፣ ፍላጐትና ዳራዊ እውቀት ያላገናዘበ ከሆነ ተማሪዎቹ እንዳይሳተፉ ያደርጋል፡፡ ይህ ክስተት በተደጋጋሚ የሚከሰት ከሆነ ተማሪዎች ለንግግር ስር የሰደደ ጥላቻ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡ ይህ እንዳይሆን መምህራን ለክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር የሚመርጡት ርዕስ ጉዳይ የተማሪዎችን ፍላጐት፣ ደረጃና ዳራዊ እውቀት ያገናዘበና የሚስብ መሆን ይገባል፡፡

**መ.ዝቅተኛና ሁሉን ያላማከለተሳትፎ** ፡- ለንግግር መለማመጃ የቀረቡት ተግባራት ሁሉንም የማያሳትፍበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህ የተሳትፎ አለመመጣጠን የተወሰኑትን አድማጭ ብቻ ስለሚያደርግ በንግግር ችሎታ መዳበር ላይ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ ለመናገር የሚያነሳሱ ሃሳቦችን በመምረጥ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የመሳተፍ እድል መስጠት ተገቢ ነው፡፡ በልምምድ ጊዜ መምህሩ ተገቢውን ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 2.13. የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የሚያዙ ተግባራት

በድሉ (2007፡89-90) መናገርን በማስተማር ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች የሚከተሉትን ተግባራት በመፍትሄነት ጠቁመዋል፡፡

**ሀ. የቡድን ሥራን መጠቀም፡-** የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራትን ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲያካሂዱ ማድረግ የሚናገሩ ተማሪዎችን ቁጥር ይጨምራል፡፡ እንዲሁም በክፍሉ ተማሪዎች ፊት ቆመው ለመናገር የሚፈሩና ጭምት ተማሪዎች በተወሰኑ ተማሪዎች አድማጭነት ንግግር እንዲለማመዱ እድል ይሰጣል፡፡ ይህን ለማድረግ እና

የሁሉንም ተሳትፎ ለማጐልበት መምህራን ትኩረት በመስጠት መከተታተል ይኖርባቸዋል፡፡

**ለ. ሳቢና አነቃቂ የመወያያ ርዕስ ወይም ጥያቄ መምረጥ፡-** ተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር የሚመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ወይም የሚዘጋጀው ጥያቄ ግልጽ፣ ሳቢ፣ ተማሪዎችን ለንግግር የሚያነሳሳና ሊያነጋግር የሚችል ሰፊ ሃሳብ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡ የተመረጠው ርዕሰ ወይም የተዘጋጀው ጥያቄ የተማሪዎችን ፍላጐት መሠረት አድርጐ ከሆነ የተማሪዎች ተሳትፎ ከፍ ይላል፡፡

**ሐ. ተግባሩን በራሳቸው የቃላት አጠቃቀም እና አገላለጽ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡-** ተማሪዎች አንድን ርዕስ ጉዳይ በተመለከተ ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ ሃሳባቸውን በራሳቸው ቃላትና የአገላለጽ መንገድ እንዲያቀርቡ ማለማመድ ተገቢ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ተማሪዎች ሊገልፁት በሚፈልጉት ጉዳይ ሙሉ ትኩረታቸውን በማሳረፍ በሚናገሩት ሃሳብና በቋንቋ አጠቃቀማቸው መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ሃሳባቸውን በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለጽ ችሎታ ተጠቅመው እንደያቀርቡ ማድረግ የንግግርን ተግባር ከባድ አድርገው እንዳያስቡት ያደርጋል፤ በራስ የመተማመን ደረጃቸውን ከፍ ያደርገዋል፡፡

**መ. የመናገር ክሂልን በሚመለከት መመሪያ ወይም ትዕዛዝ መስጠት**

በክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር ተማሪዎችን እኩል በማሳተፍ ተፈላጊውን ውጤት ማምጣት ይችል ዘንድ መመሪያና ትዕዛዞችን ተከትሎ መሄድ አለበት፡፡ ይህም የሚሆንበት ዋናው ምክንያት የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ብዙውን የልምምድ ጊዜ እንዳይወስዱ እና ጭምት ተማሪዎች እኩል ድርሻ እንዳይኖራቸው ስለሚያደርግ ነው፡፡ መምህራኑም በልምምድ ሂደት ለልምምዱ የተመለከተው መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ተግባራዊ መሆኑን መከታተል አለባቸው፡፡ ስለዚህ የመናገር ክሂልንየክፍል ውስጥ ክንውን ውጤታማ ለማድረግ በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮችን ለመቀነስ ከላይ በመፍትሄነት የቀረቡትን ነጥቦች ተግባራዊ ማድረግን መምህራን በውል ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ለመዳሰስ የተቻለው የመናገር ክሂል ምንነት፣ የመናገር ክሂልን የማስተማር ዓላማ፣የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ባህሪያት

፣ የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ የመናገር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት ፣ የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የመምህራን ሚና፣ የመናገር ክሂልን በመማር ሂደት የተማሪዎች ሚና ፣የመናገር ክሂልን ለማሰተማር የሚረዱ ብልሃቶች ፣የመናገር ክሂልን በማሰተማር ሂደት የሚጋጥሙ ችግሮች እና ችግሮቹን ለማስወገድ የሚገዙ ተግባራትን በተመለከተ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን የተገለጹትን ሀሳቦችና ማብራሪቻውን ለማስፈር ተችሏል፡፡

## 2.14. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው በሀገር ውስጥ የተደረጉ ጥናቶች የሚዳሰሱበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚው ባደረገው ቅኝት ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር በቀጥታ የሚዛመዱ ጥናቶች ባያጋጥሙትም ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ቅርበት ያላቸው ጥናቶች ለማግኘት ችሏል፡፡ ጥናታዊ ፅሑፎቹ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረቡ ሲሆኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

መንግስቱ ታደሰ (1997 ዓ.ም) "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የከፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ ምን እንደሚመስልና የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተከትለው የትምህርት ሂደቱን ማከናወን አለማከናወናቸውን መገምገም ነው፡፡ በጥናቱ ውጤትም ለደረጃው የተዘጋጀው መፅሀፍ ውስጥ ያሉት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶችን በተገቢው እና በበቂ ሁኔታ የተደራጀ እንዳልሆነ እንዲሁም ንግግርን በማስተማር ጊዜ የቀረቡት የንግግር ተግባራት የሚከናወኑበት የማስተማር ስነ-ዘዴና የክፍል ውስጥ ትግበራ ስነ-ዘዴው አመራረጥ ችግር እንዳለበት በጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ውዳዲስ ምህረቱ (2001ዓ.ም) “አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት መምህራን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች የሚሰጡትን ትኩረት ግምገማ” በሚል ርዕሰ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ ጥናት ተቋም ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበው ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል? የክፍል ውስጥ አተገባበራቸውስ? የሚሉ ዓላማዎችን ነድፎ ያጠና ሲሆን በጥናቱ የተደረሰበት ውጤትም መምህራን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተና አነስተኛ መሆኑ፣ ክሂሎቹን በማስተማር ሂደት ትኩረት የሚቀንሱ የተለያዩ ችግሮች መኖራቸውን በጥናቱ አረጋግጧል፡፡

አብርሃም ገ/ዮሀንስ (2003 ዓ.ም) “በአፋር ክልል የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና የትምህርቱ አቀራረብ” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማም አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆነው የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ምርጫና አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል መፈተሻ ነው፡፡ ጥናቱ የአማርኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር የመግለፅ ችሎታቸውን ማዳበር ይችሉ ዘንድ የተለያዩ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን ቢጠቀሙ እና የቀረቡት መልመጃዎች ለንግግር ክሂል ትምህርት ግብዓቶች ለመለማመጃነት ሊያገለግሉ ቢችሉም በቋንቋው ተጠቅመው ሀሳብን ለመግለፅና ተግባቦት የመፍጠር ብቃት የሚያዳብሩ እንዳልሆኑ አጥኚው በጥናቱ ግኝት አረጋግጧል፡፡

ጥላሁን ከበደ(2003 ዓ.ም) “የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጂታዊ አቀራረብና አተገባበር” በሚል በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት ሲሆነ የጥናቱ ዓላማም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥ ክሂልን ከመናገር ክሂል ጋር ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚተገበር ቅንጅታዊ አቀራረብን ይጠቀማሉ? ከተጠቀሙስ ከቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ አንፃር ምን እንደሚመስል መፈተሸ ሲሆን በጥናቱ የተደረሰበት ግኝትም

መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማቀናጀት ያላቸው ሚና ዝቅተኛ እንደሆነ፣ መምህራን ከተማሪዎች ችሎታ፣ ዳራና ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ይዘቶችን እንደማያቀርቡ፣ ከመማሪያ መፅሐፍ በተጨማሪ ለዓላማውተስማሚ የሆኑ አጋዥ መሳሪያዎችን እንደማይጠቀሙ በጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ይህን ጥናት ከላይ ከተገለፁት ጥናቶች ጋር የሚያመሳስለው የመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን የሚፈትሽ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን ከላይ ከተዘረዘሩት ጥናቶች የሚለየው ጥናቱ በተካሔደበት ቦታ እና በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ስነ-ዘዴ

## 3.1.የጥናቱ ንድፍ

ጥናቱ አይነታዊ ምርምርን በዋናነት የተጠቀመ ሲሆን መጠናዊ ምርምርን ደግሞ በደጋፊነት ተጠቅሟል፡፡ ጥናቱን ለማከናወን የታቀደዉ በቅይጥ ( Mixed) ዘዴ በመሆኑ መረጃዎቹ አይነታዊና መጠናዊ ናቸዉ፡፡ እነዚህ ሁለት አይነት መረጃዎች በቅይጥ ስልት ካሉት አራት ንድፎች (Creswell, 2012, 535) አንዱ በሆነዉ በገላጭ ንድፍ (Explanatory Design) የተሰበሰቡ መረጃዎችን ከሚዛመዷቸው ነጥቦች ጋር በማቀናጀት ተተንትኗል፤ ይህ ጥናትም በዚህ ንድፍ ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

ለዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጭ የሚሆኑት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች ፣ መምህራንና ተማሪዎች ሲሆኑ ፤ በመግቢያው ምእራፍ ለመግለጽ እንደተሞከረው በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ በሚገኙት ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (እነዋሪ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጅሁር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ውስጥ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን እና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በመረጃ ምንጭነት ተመርጠዋል፡፡

## 3.3 የናሙና አወሳሰድ ስልት

### 3.3.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥራቸው አራት ሲሆን ሁሉም በጠቅላይ ንሞና ዘዴ (Comprehensive sampling) በመውሰድ የጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የመምህራኑ ቁጥር አነስተኛ በመሆኑና ሁሉንም በማሳተፍ በቂ መረጃ ማግኘት ይቻላል የሚል እምነት ስላለ ነው፡፡

### 3.3.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በአማራ ክልል ውስጥ ካሉት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሰሜን ሸዋ ዞን ሞረትና ጅሩ ወረዳ ስር የሚገኙት እነዋሪ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጅሁር አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አመቺ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ትምህርት ቤቶቹ የተመረጡበት ምክንያት አጥኚው በዚህ ወረዳ የሚሰራ በመሆኑ ለጊዜ አጠቃቀም ሆነ በቂ መረጃ ለማግኘት የተሻለ ሆኖ ስላገኘው ነው፡፡

### 3.3.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ በተመረጡበት ትምህርት ቤቶች ማለትም በጅሁር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስራ አምስት እና በእነዋሪ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስራ ስምንት በድምሩ ሰላሳ ሶስት የ9ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች አሉ፡፡ በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍሎች በአማካኝ 50 የሚደርሱ ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 1650 ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን ተማሪዎች በሙሉ መጠይቁን ለማስሞላት አስቸጋሪ በመሆኑ ከጅሁር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ መቶ ሃምሳ ተማሪዎችን፤ከእነዋሪ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ መቶ ሰባ ሁለት ተማሪዎችን በድምሩ ሶስት መቶ ሃያ ሁለት(322) ተማሪዎችን እኩል እድል በሚሰጠው በቀላል የእጣ ንሞና(simple Random sampling) ስልት በሆነው በእጣ የማውጣት ዘዴ (Lottery system) እኩል መጠንና አንድ አይነት ቀለም ያላቸው ወረቀቶችን በማዘጋጀት በእያንዳንዱ ወረቀት ላይ የሚፈለገውን ያህል ቁጥርና ዜሮ በመፃፍ እኩል እኩል ከተጠቀለሉ በኋላ በሙሉ በእጣ ማውጫ ሳህን ውስጥ በማድረግ ሁሉም ተማሪዎች እየተነሱ በማውጣት ተመርጠው የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ አጥኚው በጥናቱ የሚሳተፉ የተማሪዎችን የናሙና ቁጥር ለመወሰን ( sample size) 322 መሆናቸውን የተሰላው በ(Yamane, 1967) ቀመርን በመጠቀም ነው፡፡ ማለትም፡-$n = \frac{N}{1+N(e)^2}$ , Where n= sample size , N= population size, e= is the marigin of error.

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ጥናቱ ቅይጥ (mixed) እንደመሆኑ መጠን የሚሰበሰቡት መረጃዎችም ሁለቱንም የጥናት አይነቶች የሚወክሉ ሊሆኑ ይገባቸዋል፤ ስለሆነም ይህንን አይነት መረጃ ለመሰብሰብ አራት አይነት የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ ዉለዋል፡፡ እነሱም፡- ምልከታ፣ የፅሁፍ መጠይቅ፣ የቃለ መጠይቅእና ሰነድ ፍተሻ ናቸው፡፡

### 3.4.1. ሰነድ ፍተሻ

አጥኚው ዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፉና በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱትን የመናገር ክሂል ይዘቶች  ምን ምን  እንደሆኑ ፍተሻ አካሂዷል፡፡

በመሆኑም የተማሪዉ መማሪያ መፅሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያና መርሃ ትመህርቱ ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡ በመሆኑም በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች  በተናጠል ለመገምገም ተሞክሯል፡፡ በዚህም በማስተማሪያ መሳሪያዎቹ የቀረቡት ክንውኖችን፣ ዝርዝር ዓላማዎችን፣ ይዘቶችንና መልመጃዎችን የአቀራረብ ሁኔታ ለመፈተሽ ጥረት አድርጓል፡፡

### 3.4.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ

በተጠኚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚተገበረውን  የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን ለመገምገም ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት  በጥቅም ላይ ዉሏል፡፡

የመናገር ክሂል ክንዉኖችን መምህራን በክፍል ዉስጥ እንዴት እየተገበሩት እንደሆነ ለማየት የክፍል ዉስጥ ምልከታን በዋና የመረጃ መሰብሰቢያነት ለጥናቱ ተመርጧል፡፡ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ የክፍል ዉስጥ ምልከታ ማረጋገጫ ዝርዝር (check list) ተዘጋጅቷል፡፡የክፍል ዉስጥ ምልከታ ማረጋገጫ ዝርዝሩ የተዘጋጀዉም ተዛማጅ ጥናቶች የተጠቀሙባቸዉን መሰረት በማድረግ፣የማረጋገጫ ዝርዝሮች በአማካሪ ከታዩ በኋላ የማሻሻል ስራ ተደርጎበት በስራ ላይ ዉሏል፡፡እንዲሁም በምዕራፍ ሁለት የቀረቡትን የተዛማጅ ፅሁፎችን ቅኝት መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

ሁሉም የምልከታ ነጥቦች ዝግ መጠይቆች ናቸው፡፡ይህ የሆነበት ምክንያት Dornyei (2007, 163) እንደሚሉት የተደራጀ ምልከታ በክፍል ዉስጥ የሚከናወኑ የተወሰኑ የትኩረት አቅጣጫዎችና የምልከታ ነጥቦች ላይ በማተኮር የተከናወነ በመሆኑ ነዉ፡፡

የክፍል ዉስጥ ምልከታዉን በተመለከተ ለረዳት ተመልካች መመሪያ በመስጠት የአጥኚዉንና የተጠኚ መምህራን ክፍለ ጊዜ በማመቻቸት ስለ አሞላሉ ግንዛቤ በማስጨበጥ እያንዳንዱ ተጠኚ መምህር አራት ጊዜ ምልከታ ተደርጓል፡፡ የክፍል ዉስጥ መልከታዉን ዉጤታማነት የበለጠ አስተማማኝና ከአጥኚዉ ግላዊ አመለካከት የፀዳ እንዲሆን የክፍል ዉስጥ ምልከታዉ በረዳት ተመካች እንዲታገዝ ተደርጓል፡፡

ምልከታዉ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩትን የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን አካቷል፡፡ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተዘጋጀዉ ዝርዝር ማረጋገጫ የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን የሚመለከት፣ በመናገር ክሂል ልምምድ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን፣ አፍልቆትንና ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን የሚዳስስ ሲሆን የምልከታ መረጃው የተሰበሰበው ከጥር 12/2013 ዓ.ም እስከ ግንቦት 30/2013 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ ነው፡፡

### 3.4.3 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጋር ሲነጻጸር ጊዜን፣ ጉልበትን እና ገንዘብን ቆጣቢ በመሆኑና የመላሾችንም ማንነት ስለማይገልጽ መላሾች አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ስለሚያበረታታ በምርምር መስኮች የበለጠ ጥቅም ላይ እንደሚውል (ያለው 2004፣ 148) ጠቅሰዋል፡፡ ስለሆነም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የጽሁፍ መጠይቁ መሰረታዊ ዓላማ በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ የሚገኘውን መረጃ ለማገናዘብና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች የቀረበዉ የጥናቱን ዉጤት ከፍ ለማድረግ ነዉ፡፡

ለመምህራን የተዘጋጀዉ የፅሑፍ መጠይቆች ለተተኳሪ መምህራንና ለተጠኚ ተማሪዎች ተበትኖ እንዲሞሉ ተደርጎ መረጃዉን በመሰብሰብ በትንታኔ ቀርቧል፡፡ ለተማሪዎቹም አጥኚዉ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ዉስጥ በመገኘት አጠቃላይ ዓላማ ገለፃ በማድረግ እንዲሞሉ·ተደርጎ መረጃዉ ተሰብስቦ በትንታኔ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 3.4.4 ቃለ መጠይቅ

እንደ Dorneyei (2007) አገላለፅ “ ቃለ መጠይቅ አንድ ተመራማሪ መረጃ ከሚያገኝባቸው መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ከባለ ጉዳዮቹ ጋር በግንባር በመገናኘት በቃል የሚደረግ ጥያቄ ነው፡፡” በማለት ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ቃለ መጠይቅ ለጥናቱ ደጋፊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተመረጠ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን ቃለ መጠይቁ የተደረገው ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ መምህራን ነው፡፡አጥኚው መረጃውን ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ የተጠቀመበት ምክንያት ጥያቄዎችን ለማብራራት፣ግልፅ ያልሆኑ ምላሾችን ይበልጥ ግልፅ እንዲሆኑ ለማድረግና የተፈለገውን መረጃ ለማስገኘት ስለሚያስችል ነው፡፡

## 3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት

የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሲዘጋጁ የተለያዩ ቅደም ተከተሎችን በማክበር ነዉ፡፡ በመጀመሪያ ከጥናቱ ጋር ተቀራራቢ የሆኑ የቀደምት ጥናቶች የተጠቀሙባቸዉን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፍተሻ ተደርጓል፡፡ ለዚህ ጥናት ተስማሚና ትክክለኛ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የክፍል ውስጥ ምልከታ፣የጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ እነዚህ መጠይቆች ከጥናቱ ንድፈ ሐሳባዊ መሰረትና ከተዛማጅ ጽሁፎቹ ላይ ከተገኙ መረጃዎች በመነሳት የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ከዚያም በተለያዩ ሶስት (TeAm-M.A) የተማሩ መምህራን እንዲገመገሙ ተደርገዋል፡፡ በመጨረሻም ከአማካሪ ጋር በመመካከር ማስተካከያዎች ተደርገው ከተዘጋጁ በኋላ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

## 3.6. የመረጃ መተንተኛ ስልት

ጥናቱ የተከናወነው በቅይጥ ዘዴ በመሆኑ የሚሰበሰቡት መረጃዎች አይነታዊና መጠናዊ ናቸዉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ መረጃዎች ቅይጥ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በቅይጥ የምርምር ስልት ውስጥ ካሉት አራት ንድፎች በገላጭ ዘዴ ተብራርቷል፡፡ ዘዴው የተመረጠበትም ምክንያት መረጃዎቹን ርስበርስ እያስተሳሰሩ ለመተንተን ስለሚያስችል ነው፡፡(Dornyei Z. 2007.158) የክፍል ውስጥ ምልከታን

ለጥናት ውጤት አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ምልከታው በቃለመጠይቅና በጽሁፍ መጠይቅ መደገፍ እንዳለበት ይገልፃሉ፡፡ በዚህም የክፍል ውስጥ ምልከታው የሚገኙትን መረጃዎች ከሌሎች የመረጃ ምንጮች ጋር በመመሳከር በአሃዛዊና በገለፃዊ የአቀራረብ ስልት የሚቀርብ ሲሆን ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በመላሾች ላይ የማጣራት፣ ኮድ የማድረግ ሂደት ከተከናወነ በኋላ መረጃዎቹ በመቶኛ ተሰልተው የአሃዞቹ አንድምታ በገለፃ መልክ ተብራርቷል፤ከዚያም በቃለመጠይቅና በአይነታዊ የመረጃ ስልት ማለትም በገለፃ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ

በዚህ ምዕራፍ ስር በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብን ፣ የመምህራን የመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን ፣መምህራን ተማሪዎችን የተሻለ የመናገር ችሎታ እንዲኖራቸው ስለሚያደርጉባቸው ተግባራት ፣ የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የመምህራን ሚና ምን ምን እንደሆኑ፣መምህራን የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ጊዜ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን እና የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎችን በተመለከተየተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነዋል፤የጥናቱ ግኝትም ተብራርቷል፡፡ በምዕራፍ ሦስት እንደተገለፀው ከክፍል ውስጥ ምልከታ፣ከፅሑፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ እንዲሁም ከሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ከሚዛመዱቸው ነጥቦች ጋር በማቀናጀት በሶስት ጎንዮሻዊ (Triangulation) ስልት ተተንትነዋል፡፡የዋናው ጥናት ትንተና ከመቅረቡ በፊት የመምህራን አጠቃላይ መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 4.1. የመምህራን አጠቃላይ መረጃ

**ሰንጠረዥ1፡-**የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠሰቃላይዳራዊ መግለጫ

| ተ/.ቁ | የትምህርት ቤት ስም | መምህር | ፆታ | እድሜ | የትም/ት ደረጃ | የትምህርት መስክ | | የማስተማር ልምድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | አብይ | ንዑስ | |
| 1 | እነዋሪሚሊ/መሰ/አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | ሀ | ወ | 38 | ቢ.ኤ ዲግሪ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 16 |
| | | ለ | ሴ | 44 | ቢ.ኤ ዲግሪ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 20 |
| 2 | ጅሁር አጠቃላይ | ሐ | ወ | 42 | ቢ.ኤ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 18 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | | | | ዲግሪ | | | |
| | | መ | ሴ | 36 | ቢ.ኤ ዲግሪ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 14 |

ከሰንጠረዥ አንድ መመልከት እንደሚቻለው ጥናቱን ለማከናወን ያመች ዘንድ የመምህራን ዳራ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ጥናቱ የተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች ሁለት ሲሆኑ፣ በጥናቱ የተሳተፉት ሁለት ወንድ መምህራን እና ሁለት ሴት መምህራን በድምሩ አራት መምህራን መሆናቸውን ሰንጠረዡ ያሳያል፡፡

ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊዎች መምህራን በመጀመሪያ ዲግሪ የሰለጠኑ ናቸው፡፡ እንዲሁም አራቱም የጥናቱ ተሳታፊዎች ከ14-20 ዓመትየስራ ልምድ አላቸው፡፡ በጥናቱ የተሳተፉት ሁለት ወንድ መምህራንና ሁለት ሴት መምህራን በአጠቃላይ አራት መምህራን መሆናቸውንም ሰንጠረዡ ያስረዳል፡፡

የመምህራን ዳራዊ መግለጫ እንደሚያስረዳው ፣ሁሉም የጥናቱተሳታፊ መምህራን ሰከአስራአራት አመት በላይ በመምህርነት ሙያ ያገለገሉ ናቸው ፡፡ ይህ አገልግሎት ደግሞ መምህራንን በመምህርነትና ከዚያ በላይ ባሉ የማዕረግ ደረጃዎች የሚያደርስ በመሆኑ ለጥናቱ የሰጡትን መረጃ ሊያዛባ የሚችል ተላውጦ እንደማይኖር ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጅ በዚሁ ጥናት የተጠኚ መምህራን የአገልግሎት ዘመን፣የትምህርት ደረጃና ዕድሜ ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የለውም፡፡ ነገር ግን በጥናቱ የተሳተፉትን መምህራን አጠቃላይ ገፅታ ለማስተዋወቅ ይረዳል ተብሎ በአጥኚው ስለታመነበት ከፍ ሲል በተገለፀው መልክ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

## 4.2. ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ጥናት የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች የምንላቸው የዘጠነኛ ክፍል የተማሪውን መፅሐፍ፣የመምህሩ መምሪያና መርሃ ትምህርቱን ያጠቃለሉ ናቸው፡፡የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች የቋንቋ ትምህርት ሂደትን የተሳካ ለማድረግ የሚጠቅሙ የትምህርትመሳሪያዎች ናቸው፡፡

Nunan(1989, 105)የትምህርት መሳሪያዎች በቋንቋ ትምህርት ክፍል እና በእውኑ ዓለም ያለውን ግንኙነት ግልፅ የሚያደርጉ እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን የማስተማሪያ መሳሪያዎች እያንዳንዳቸው መናገርን በማስተማር ሂደት እውን የሚሆኑ ዓላማዎችን፣ይዘቶችን፣ክንውኖችና ግምገማዎችን ያካተቱ መሆናቸው ግልፅ ነውበማለት አብራርተዋል፡፡

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት በ2004 ዓ/ም ታትሞ በተግባር ላይ የዋለውን የዘጠነኛ ክፍል የተማሪው መፅሐፍ ፣የመምህሩ መምሪያንና መርሃ ትምህርቱን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም ከአራት የቋንቋ ክሂሎች አንዱ የሆነውን የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ዓላማቸው አንፃር ትንተናና ግምገማ ተደርጓል፡፡

አጥኚው የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችንና ዓላማዎቻቸውን ተስፋዬ(1981) ላይ ካስቀመጡት የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ባህሪያት አንፃር የዘጠነኛ ክፍል የመናገር ክሂል ትምህርት መርሃ ትምህርቱን፣የመምህሩ መምሪያና የተማሪውን መማሪያ መፅሐፍን በመፈተሽ እንደሚከተለው ገምግሟል፡፡

1. **ተገቢነት**፡-በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በቀረቡት አስር ምዕራፎች ውስጥ በሁሉም ምዕራፎች የንግግር ትምህርት ተካቷል፡፡በመሆኑም በዚህ ክፍል ለክሂሉ ተገቢው ትኩረት እንደተሰጠው መረዳት ይቻላል፡፡የአላማ ተገቢነትን ስንመለከት በአስሩም ምዕራፎች የቀረቡት የንግግር ትምህርት ዓላማዎች እያንዳንዳቸው በንግግር ክሂል ሊዳብሩ የሚገባቸውን አበይት የንግግር ትምህርት ንዑሳን ክሂሎች ይዘዋል፡፡ እንዲሁም የአላማዎቹ አነዳደፍ ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት እንዲሳተፉ የሚያደርጉ በመሆናቸው ተገቢ ናቸው፡፡ በተያያዥነት ከንግግር ፋይዳ አብዛኞቹ የምዕራፎቹ ተግባራት አንፃር የተግባራቱን ተገቢነት ስንፈትሽ የተቀመጡት ተግባራት ተማሪዎች በዚህ ክፍል ደረጃ ከሚኖራቸው ልምድና ችሎታ አንፃር ተገቢ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የተማሪዎችን ስሜትና ፍላጎትበማነሳሳት ረገድም ተግባራቱ በየምዕራፉ አዳዲስ ስልቶችና ርዕሰ ጉዳዮችን ስለሚያነሱ ተማሪዎች በመነሳሳት መረጃን እየፈለጉ በማምጣት በክፍል ውስጥ ለመተግበር ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ የመናገር ክሂል

ትምህርት ተግባራቱ ከዓላማ ፣ከፋይዳና ከተማሪዎች ዕድሜና ችሎታ ጋር ተገቢ ሆነው ተቀርፀዋል፡፡

2. **ግልፅነት፡-** በዚህ ክፍል የቀረቡት የንግግር ትምህርት ዓላማዎችና ተግባራት ከሰዋሰዋዊ መዋቅር እና ከቋንቋ አጠቃቀም አንፃር ግልፅ ናቸው፡፡የቀረቡት መመሪያዎች፣ትዕዛዛትና መግለጫዎች የተማሪዎችን የመረዳት ሂደት የማያደናቅፉና ወደ ተግባር የሚመሩ ናቸው፡፡ ዓላማዎቹም በመምህሩ መምሪያም ሆነ በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ የተቀመጡት ለመረዳት ግልፅ ናቸው፡፡
3. **ተለጣጣቂነት፡-** የቀረቡት የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች እርስ በርስ ተከታታይነት ያላቸውና የተለጣጠቁ ናቸው፡፡ተማሪዎች በተዋረድ እርስ በርስ በሚከታተሉና ተገቢውን የመልመጃ እድገት ሂደት በተከተሉ ክንዋኔዎች እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡ ተግባራቱ ከተራ ወደ ውስብስብ ይሄዳሉ፡፡ተማሪዎች በቀላሉ ሊናገሩባቸው ከሚችሉባቸው አውዶች ወደ ውስብስብና ቅድመ ዝግጅትን ወደሚጠይቁ መረጃ የመፈለግ፣የመሰብሰብና የማደራጀት ሂደት እያደጉ እና እየሰፉ የሄዱ ናቸው፡፡ የተማሪዎችን አንደበት ርቱዕነት ማሳደግ በተመለከተ በየምዕራፉ ተማሪዎች ወደ ተወሳሰበና ከፍታ ወዳለው የንግግር ብቃት የሚያደርሱ ተግባራት ስለቀረቡላቸው በምዕራፎቹ ማብቂያ ላይ ከክፍሉ ደረጃ ወደሚጠበቀው የንግግር ብቃት ለመድረስ አይቸገሩም፡፡
4. **ተተግባሪነት፡-**በሁሉም ምዕራፎቹ ውስጥ የቀረቡት ተግባራት ከተተግባሪነታቸው አንፃር ሲፈተሽ አብዛኞቹ ጥሩ ናቸው፡፡ይኸውም ተማሪዎች በቅድመ ተግባራት በክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ የሚከውኗቸው ተግባራት ለተማሪዎች ምቹና ተደራሽ ናቸው፡፡ሆኖም በአንዳንድ ምዕራፍ ማለትም በምዕራፍ አምስትና ስምንት ላይተማሪዎችን መረጃ እንዲሰበስቡ ሲታዘዝ ከመገናኛ አውታሮች እና ከቴሌቭዥን የሚገኙ በመሆናቸውና መፅሐፉ ደግሞ በሀገር ደረጃ የተሰራጪና ለማስተማር የተቀረፀ በመሆኑ በተለይም የተጠቀሱትን የመረጃ አውታሮች በቅርብ ለማያገኘው የገጠር አካባቢ ተማሪ ተተግባሪ አይሆንም፡፡መፅሃፉም እነዚህን የመረጃ አውታሮች ሲጠቁም ሌሎች አመራጮችን አልጠቆምም፡፡ ስለሆነም በከተማ ብሎም በገጠር አካባቢ ለሚገኙ ተማሪዎች የተተግባሪነት ችግር ሊገጥመው ይችላል በማለት ጥናቱ ገምግሟል፡፡ለምሳሌ፡-በምዕራፍ ስምንት ላይ

ስለ ሸንኮራ አገዳ ተክል አመራረትና በፋብሪካ ያለውን ሂደት ተረድቶና መረጃ አጠናቅሮ ወደ ክፍል ለመግባት ያለውን ሂደት መጥቀስ ይቻላል፡፡

5. **አሳታፊነት፡-**በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በቀረቡት አስር ምዕራፎች በሁሉም የመናገር ክሂል ትምህርት መካተቱን መገንዘብ ተችሏል፡፡ይሁን እንጅ ከአሳታፊነት አንፃር ተግባራቱ ሲመዘኑ በአብዛኛው በቡድን የሚሰሩና በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ትዕዛዛት ይበዛሉ፡፡ ይህ አሳታፊነቱን ቢያሳየንም በንግግር እያንዳንዱ ተማሪ መናገሩንና ልምምድ ማድረጉን ለመከታተል መምህሩም ጊዜ ስለሚያጥረው ተማሪዎች በቡድን ስራ እንዲዋጡ አድርጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ቢያንስ በጥንድ የሚያቀርቡበት ወይም የሚነጋገሩበትና መምህሩምየሚከታተሉበት ሁኔታ አልተመቻቸም፡፡

## 4.3. የመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር መረጃ ትንተና

ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ዋናጥቅማቸው ለአጥኚው ተጠኚዎች የተገበሩትን ነገር ከሚነግሩት ይልቅ እራሱ አጥኚው በቀጥታ ማየት መቻሉ ነው፡፡ በዚህ አይነት መንገድ የሚገኙ መረጃዎች ከሁለተኛ ምንጭ ከሚገኙ መረጃዎች የበለጠ ተጨባጭ እንደሆኑ(Dorneyi,2007) ገልፀዋል፡፡ በዚህ ሀሳብ መነሻነት የተደራጀ የምልከታ ቅፅ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት ተተኳሪ ነጥቦች መተግበር አለመተግበራቸውን መከታተል የተቻለ ሲሆን የእያንዳንዱን የመናገር ክሂል የመከታተያ ነጥብ አተገባበር ከመምህራንና ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ እና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ እንዲሁም ከሰነድ ፍተሻ ጋር እየተዛመደ መረጃው እንዲሚከተለው ተተንትኗል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡- የመምህሩ/ሯ/ የክፍል ውስጥ መናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የምልከታ መከታተያ ነጥቦች | የምልከታው አማራጮች በቁጥርና በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ/ ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ | በ% |
| 1 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪው መመሪያ መፅሐፍ መሰረት ያደርጋል፡፡ | 3 | 75 | 1 | 25 | | | | |
| 2 | የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቱ የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ማገናዘቡን ያረጋግጣል፡፡ | | | | | 1 | 25 | 3 | 75 |
| 3 | በተማሪዎችና በመምህሩ ዘንድ ግልፅና ውስን ዓላማ ይዞ ይገባል፡፡ | | | 3 | 75 | | | 1 | 25 |
| 4 | መነቃቃትን ለመፍጠር ከርእሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎችን ይጠይቃል፡ | | | | | 1 | 25 | 3 | 75 |
| 5 | ተማሪዎች ለሚያከናውኑት ተግባራት ግልፅ መመሪያ ይሰጣል፡፡ | | | 3 | 75 | 1 | 25 | | |

ከላይ በሰንጠረዥ ሁለት የምልከታ መከታተያ መስፈርት ከተሰጠው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው 3(75%) የሚሆኑት መምህራን“ ሁል ጊዜ ተ” በሆነ መልኩ የመናገር ክሂል ትምህርትን ለተማሪዎች የሚያቀርቡት የተማሪውን መማሪያ መፅሐፍንመሰረት አድርገው የተገበሩ መሆናቸውን መመልከት ተችሏል፡፡ሌሎቹ 1(25%)ቱ መምህራንም“በከፍተኛ” ሁኔታ የተማሪውን መማሪያ መፅሐፍንመሰረት አድርገው የተገበሩ መሆናቸውን በምልከታው መረዳት ተችሏል፡፡

እንዲሁም በሰንጠረዥ ሁለት በተራ ቁጥር ሁለት ላይ ለቀረበው የምልከታ መከታተያ መስፈርት ከተሰጠው ምላሽ መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ 3(75%)ያህሉ መምህራን የተገበሩት የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘት የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ የማገናዘብ ሁኔታ“ዝቅተኛ”መሆኑን ከምልከታው መረዳት ተችሏል፡፡አንዱ መምህር 1(25%)ግን የመናገር ክሂል ትምህርቱን ይዘት ከተማሪዎች የትምህርት ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን“መካከለኛ”በሆነ መልኩ ያገናዘበ ትምህርት መስጠቱን መመልከት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡-በተማሪው መፅሐፍ ውስጥ በገፅ 140 ላይ “በሸንኮራ አገዳ ተክል ስኳር እንዴት እንደሚመረት በፋብሪካ ውስጥ ወደ ስኳር ምርትነት እንዴት እንደሚለወጥ ንግግር አድርጉ፡፡”የሚለውን የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘት ትእዛዝ አንዱ መምህር ብቻ ይዘቱን በራሳችሁ በማስተካከል በአካባቢያችሁ ከሚመረቱ ምርቶች እንዱን መርጣችሁ ለምግብነት እስከሚውል ድረስ ያለውን ሂደት በማስታወሻ ይዛችሁ ንግግር አድርጉ በማለት ትእዛዝ ሲያስተላልፉ ታይተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከመረጃ ትንተናው መረዳት እንደሚቻለው ሁሉንም ተማሪዎች ያማከለ ወይም አሳታፊ የመናገር ክሂል ትምህርት አብዛኛዎቹ መምህራን አልመረጡም ወይም ተማሪዎቹ በሚገባቸውና በአቅማቸው ልክ የሆነ እና ዳራዊ እውቀታቸውን መሰረት ያደረገ እንዳልሆነ ከምልከታው መረዳት ተችሏል፡፡ ይህንን ሃሳብ በተመለከተ (Fayzeh,2012)እና (Widowson,1990)እንዳሉት “ንግግርን ለማስተማሪያነት የሚቀርቡ ይዘቶች ከተማሪዎች እድሜ፣ዳራዊ እውቀትና ከትምህርት ደረጃቸው ጋር የተጣጣመ መሆን ይገባቸዋል፡፡” በማለት ገልፀዋል፡፡

ሌላው በሰንጠረዥ ሁለት በምልከታ ተራ ቁጥር ሶስት ለቀረበው የምልከታ መከታተያ ነጥብ በመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ስር በምልከታው ለማየት የተሞከረው መምህራን የእለቱን የመናገር ክሂል ትምህርት ከማቅረባቸው በፊት ግልፅና ውስን ዓላማን ይዞ ወደ ክፍል ከመግባት አንፃር ምን ያህል ነው? የሚል ሲሆን ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ማለትም 3(75%) ያህሉ በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡትን ትምህርት ግልፅእና ውስን ዓላማን “በከፍተኛ” ሁኔታ ይዘው ሲገቡ 1(25%)ያህሉ ደግሞ ለተማሪዎቻቸው ግልጽ እና ውስን ዓላማ ይዞ በመግባት በእለቱ የሚተገበሩትን የንግግር ተግባራትን ለተማሪዎች አያስተዋውቁም፡፡ስለሆነም አብዛኞቹ መምህራን የእለቱን

ትምህርትከማስተማራቸው በፊት ለተማሪዎቹ ዓላማን የማስተዋወቁን ሁኔታ እንደታየው“ዛሬ የምትማሩት ይህ ነው ፤ከዚህ ትምህርት የምታገኙት ጥቅም ይህ ነው፡፡”በማለት 3(75%) ያህሉ ዓላማን ሲያስተዋውቁ 1(25%)ቱ መምህራን ግን ለተማሪዎች የትምህርቱን ዓላማ በግልፅ እንደማያስተዋውቁ ለመመልከት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በሰንጠረዥ ሁለት ለተራ ቁጥር አራት በቀረበው የምልከታ መከታተያ ነጥብ መስፈርት ከተሰጠው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለውከአንድ መምህርት ውጭ ተማሪዎችን መነቃቃትን ለመፍጠር ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎችን ለመጠየቅ የሞከረ አልነበረም፡፡አብዛኛዎቹ መምህራን 3(75%)ያህሉ የተማሪዎችን ተራ ቁጥር በመጥራት የተሰጣቸውን ምንባብ ሸምድደው በቃል እንዲያቀርቡ ማድረግ፣በቡድን ስራ የተሰጡትን ርእስ መሰረት አድርገው የተለማመዱትን ጭውውት በቀጥታ ለጓደኞቻቸው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማበረታታት እንጂ በባለፈው ጊዜ ስለምን እንደተማሩ፣የእለቱ ትምህርት ምን እንደሆነ ምንም አይነት የማነቃቃት ተግባራትሲከውኑአልታዩም ፡፡በዚህ የተነሳ ወደዋናው ስራ እንዲገቡ ባለመደረጋቸው እርስ በርስ መደማመጥ የሌለበት ሁኔታ እና ተማሪዎች ንግግሩን ለማድረግ ዝግጁ አለመሆናቸው ስርአቱን የጠበቀ ክንውን እንዳይፈፅሙ አድርጓቸዋል፡፡ስለዚህ ይህ እንዳይሆን የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ዝንባሌና አቅም አገናዝቦ ካለፈው የትምህርት ይዘት እና ክንውን ጋር የእለቱን ትምህርት ለማያያዝ ያመች ዘንድ ማነቃቂያ ቸል ሊባል አይገባውም፡፡

በመጨረሻም በዚሁ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር አምስት ለቀረበው የምልከታ መከታተያ መስፈርት ደግሞ መምህራን ተማሪዎች ሰለሚያከናውኑት ተግባራት ግልፅ መመሪያ የመስጠት ሁኔታን በተመለከተ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር 3(75%) የሚሆኑት መምህራን “ከፍተኛ” በሆነ መልኩ ለተማሪዎች ስለሚያከናውኑት ተግባራት ግልፅ መመሪያ ሲሰጡ ታይተዋል፡፡ 1(25%)ቱ ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ 1(25%)ቱ ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ በምልከታው ለማየት ተችሏል፡፡

ይህንን ሃሳብ አስመልክተው Ur(1996፡121) “በክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር ሲከዎን ተማሪዎችን እኩል ለማሳተፍ እና ተፈላጊውን ውጤት ለማምጣት ይቻል ዘንድ ግልፅ መመሪያንና ትዕዛዞችን ተከትሎ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ስለሆነም መምህራንለተማሪዎቻቸው የሰጡትን መመሪያና ትእዛዝ ተግባራዊ መሆኑን መከታተል አለባቸው ፡፡ስለዚህ ተማሪዎች ስለሚያከናውኑት ተግባራት ከመነሻው

ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ካላቸው ተግባራቱን በሚያከናውኑበት ጊዜ ግራ የመጋባት ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡"በማለት ገልፀዋል፡፡

የመምህራንን የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ክንውኖች ለመፈተሽ ከክፍል ውስጥ ምልከታ በተጨማሪ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የዋሉት የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ፣የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ እና ሰነድ ፍተሻናቸው፡፡የተማሪዎቹን የፅሁፍመጠይቆቹን እንዲሞሉ ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች የተወሰዱት ተማሪዎች ብዛት ወንድ 150 ሴት 172 በድምሩ 322 ናቸው፡፡

መግለጫ ፡- ለተማሪዎች የቀረቡት የጽሁፍ መጠይቆች የምርጫዎቹ ዝርዝር ሀ፣ለ፣ ሐ፣መ፣ሲሆን ለማገናዘቢያ አባሪ"ሶስት" ን ይመልከቱ፡፡

**ሰንጠረዥ3፡-** የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በሚመለከት የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 1 | መምህሩ/ሯ/የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችን ሲያስተምሯችሁ የመማሪያ መፅሐፉን መሰረት የማድረጉ ሁኔታ ምን ያህል ነው? | 280 | 86.9 | 42 | 13.1 | - | - | - | - |
| 2 | መምህሩ/ሯ/በአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል ትምህርት ክፍለ ጊዜ | 200 | 62.1 | 122 | 37.9 | - | - | - | - |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዓላማውን የማስተዋወቅ ሁኔታ ምንያህልይገለፃል/ትግ ልፃለች? | | | | | | | | |
| 3 | መምህሩ/ሯ/ የእለቱን የመናገር ክሂል ትምህርትከመጀመራቸ ውበፊት ተማሪዎችን የማነቃቃታቸው ሁኔታእንዴት ይገለፃል/ትግልፃለች? | - | - | 100 | 31.1 | 222 | 68.9 | - | - |
| 4 | መምህሩ/ሯ/ የመናገር ክሂል ትምህርት ከመጀመራቸው በፊትአጭርና ግልጽ መመሪያ ምን ያህል ይሰጧችኋል? | 122 | 37.9 | - | - | 200 | 62.1 | - | - |

በሰንጠረዥ ሶስት ለጥያቄ ቁጥር አንድ ከተሰጠው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው 280(86.9%)የሚሆኑት ተማሪዎች “ሁል ጊዜ” የሚማሩበት የአማርኛ ቋንቋ መፅሐፍ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን መሰረት አድርገው እንደሚያስተምሯቸው ሲገልፁ 42(13.1%)ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ “አብዛኛውን ጊዜ”የሚለውን አማራጭ መርጠው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡በመሆኑም አብዛኛዎቹ መምህርን የመናገር ክሂል ትምህርትን ስያስተምሩ በመማሪያ መፅሃፋቸው ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች መሰረት ማድረጋቸውን ከተማሪዎች ምላሽና ከምልከታው ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚሁ ሃሳብ ጋር አያይዘው Harmer (2001፡257) እንዳሉት“የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የቋንቋ መማር ማስተማርን የሚመሩ የቋንቋ ትምህርት መነሻና መድረሻውን የሚጠቁሙ ፣የተለያዩ ይዘቶችን በምሳሌ አስደግፊው የሚያቀርቡ መልመጃዎችንና የተለያዩ ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎች እንዲለማመዱ

የሚያደርጉ፣በአጠቃላይ መሰረታዊ እውቀትና የተለያዩ ፅንሰ ሀሳቦችን ለተማሪው የሚያስጨብጡ፣ለመምህሩም ስራ አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡” በማለት ገልፀዋል፡፡

እንዲሁም በዚሁ ሰንጠዥ በሁለተኛው ጥያቄ ላይ የቀረበው መምህራን በአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል ትምህርት ክፍለ ጊዜ አላማውን የማስታዋወቅ ሁኔታ እንዴት ነው?የሚል ሲሆን ለዚህ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 200(62.1%)“ሁል ጊዜ” አላማውን ያስተዋውቁናል በማለት ምላሽ ስሰጡ 122(37.9%)ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ “አብዛኛውን ጊዜ”በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ከዚህ የመረጃ ትንተና መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርት ሲያስተምሩ አላማውን እንደሚያስተዋውቁ ከተማሪዎች ምላሽእና ከምልከታው መገንዘብ ተችሏል፡፡

እንዲሁም በሰንጠረዥ ሶስት ከላይ ለጥያቄ ሦስት መጠይቅ ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ 100(31.1%)ያህሉ ተማሪዎች መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን ከማቅረባቸው በፊት በተለያዩ መንገዶች ተማሪዎችን “አብዛኛውን ጊዜ”እንደሚያነቃቋቸው ሲገልፁ 222 (68.9%) ያህሉ ተማሪዎች ግን “አልፎ አልፎ፡ያነቃቁናል”በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል ፡፡ስለዚህ ከተማሪዎቹ ምላሽ መረዳት የሚቻለው የእለቱ ትምህርት ከመቅረቡ በፊት አብዛኛዎቹ መምህራን አልፎ አልፎ የተማሪዎቻቸውን የቅድመ እውቀት ከእለቱ ትምህርት ጋር በማዛመድና የእለቱ ትምህርት በምን ዙሪያ እንደሚያጠነጥን ፍንጭ በመስጠት የተማሪዎችን ትኩረት ለመሳብ ጥረት እንደሚያደርጉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ሌላው ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ የመምህራን የመመሪያ አሰጣጥን የሚመለከት ነው ፡፡ለዚህ ጥያቄ 200 (62.1%)ያህሉ ተማሪዎች “ሁል ጊዜ መመሪያ ይሰጣሉ”የሚል መልስ ሲሰጡ 122 (37.9%)ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ “አንዳንድ ጊዜ ”መመሪያ ይሰጣሉ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ይህን ሃሳብ በተመለከተ Ur(1996፡ 121)እንደገለፁት “ መምህራን ወደ እለቱ የመናገር ክሂል ትምህርት ተግባር ከመግባታቸው በፊት አላማውን፣አስፈላጊነቱን ፣ጠቀሜታውን በሚመለከት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅ እና አጭር መመሪያ መስጠት ተማሪዎቹ ግራ የመጋባት ስሜት እንዳይፈጥርባቸውና ክንውኑ በተሳካ ሁኔታ ተግባራቸውን እንዲቀጥሉ ይረዳቸዋል” ይላሉ፡፡ከዚህ አንፃር ሲታይ የመምህራኑ የትምህቱ አቀራረብ በአብዛኛዎቹ ተማሪዎች እይታ ሁል ጊዜ እንደሚተገበር

መረዳት ተችሏል፡፡የክፍል ውስጥ ምልከታው መረጃ ውጤትም ይህንኑ ሃሳብ አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡-የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በሚመለከት ከመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | ሁልጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | በፍፁም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 1 | የመናገር ክሂል ትምህርት የሚተገብረው ለደረጃው የተዘጋጀውን የመማሪያ መፅሐፍ መሰረት በማድረግ ነው ፡፡ | 3 | 75 | 1 | 25 | - | - | - | - |
| 2 | ወደዋናው የመናገር ክሂል ተግባር ከመግባቴ በፊት ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅ እንዲነቃቁ አደርጋለሁ ፡፡ | - | - | 3 | 75 | 1 | 25 | - | - |
| 3 | የመናገር ክሂል ትምህርትን በማስተምርበት ወቅት ቀድሜ ዓላማውን አስተዋውቃለሁ፡፡ | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - | - | - |

ከሰንጠረዥ አራት መረዳት እንደሚቻለው በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ያሉ የዘጠነኛ ክፍል መምህራን ለቀረበላቸው የፅሁፍ መጠይቅ 3(75%) የሚሆኑት መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን መጠይቅ ለቀረቡት አራት መምህራን ለደረጃው በቀረበው የመማሪያ፣ማስተማሪያና መርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ የመናገር ክሂል ትምህርት ተግባራትን ቢጠቅሱልኝ?ተግባራቱ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚያዳብሩ ናቸው ? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርቦላቸው ሁሉም መምህራን በመፅሐፍ ውስጥ ያሉትን ተግባራት ክርክር ፣ውይይት፣ጭውውት፣የቃል ጥናት ወዘተ ናቸው በማለት ከዘረዘሩ በኋላ 3(75%)ያህሉመምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚያዳብሩ ናቸው በማለት ሲገልፁ 1(25%) ግን በመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ያሉትን የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ላይ ብቻ ማተኮር በቂስላልሆኑ ከመማሪያ መፅሐፍ ወጣ በማለት ተማሪዎችን የሚያነሳሳ ይዘት በመቅረፅእንደሚያስተምሩ ገልፀዋል፤ይህም በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታው ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም“ ለመናገር ክሂል ትምህርት የቀረበው ይዘት የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያማከለ መሆኑን ይገመግማሉ?”ለሚለው የቃል ጥያቄ 3(75%)ያህሉ መምህራን ምንም አይነት ግምገማ እንደማያደርጉ በቀጥታ በመማሪያ መፅሐፋቸውላይ ያለውን ይዘት መሰረት በማድረግ በመማሪያው መሰረት ወደ ተግባሩ እንዲገቡ ንግግር እንዲያቀርቡ እናደርጋለን በማለት ለቃለ መጠይቁ ምላሽ ሲሰጡ 1(25%)ቱ ብቻ አልፎ አልፎ እገመግማለሁ በማለት ገልፀዋል፡፡የአገማገሙ ሁኔታም በመፅሃፋቸው ላይ ያለው ተግባር ለተማሪዎቹ ግልፅያልሆነ እና የማያውቁት ከሆነ እንደ አካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡ይህን ሳደርግ ደግሞ የተማሪዎቹን ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ ያማከለ እንዲሆን ጥረት አደርጋለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ንግግር የሚያደርጉበትን ርእስ እራሳቸው በፈለጉት እና በሚመቻቸው መንገድ እንዲያቀርቡ አመቻቻለሁ በማለት ገልፀዋል፡፡ይህንን ሀሳብ በተመለከተ Ur(1996፡50) “ተማሪዎች በራሳቸው ጥሩና መጥፎ ገጠመኝ ዙሪያ በአካባቢያቸው ያለውን ባህል፣ልምድና እውቀት መነሻ በማድረግ የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን መርጠው የሃሳብ ልውውጥ ቢያደርጉ መልካም ውጤት ሊገኝ ይችላል” በማለት ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጅ አብዛኛዎቹ መምህራን ይህን ተግባር ለመከወን የሚያደርጉት ጥረት አነስተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ጥረታቸውንም በሰጡት

የቃል መጠይቅ ምላሽ ብቻ ሳይሆን በምልከታ እንዲሁም ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ሌላው ሁለተኛው ጥያቄ መምህራን ወደዋናው የመናገር ክሂል ተግባር ከመግባታቸው በፊት ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎችን በማነቃቃት ደረጃ 3(75%)ያህሉ መምህራን "አብዛኛውን ጊዜ"ተግባሩን ሲተገብሩት 1(25%) ቱ ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚተገብሩት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በዚሁ ሰንጠረዥ ሶስተኛው ጥያቄ ደግሞ ከመናገር ክሂል ትምህርት በፊት ስለንግገር አቀራረብ ተማሪዎች አላማውን እንዲያውቁ ያደርጋሉ?ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሰጡት 1(25%) ያህሉ መምህራን "ሁልጊዜ " አላማውን ቀድሜ አስተዋውቃለሁ ሲሉ 3(75%)ቱ መምህራን ደግሞ "አብዛኛውን ጊዜ"አላማውን ቀድሜ አስተዋውቃለሁ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ መምህራን በሰነድ ፍተሻ እንደተረጋገጠው በእለታዊ የትምህርት እቅዳቸው ላይ የዚህ ትምህርት ዋና አላማ የመናገር ክሂልን ማሻሻል፣ተማሪዎች ከሚያውቁት ታሪክ በመነሳት ንግግር እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው ወዘተ የሚል ዓላማ በእቅዳቸው ላይ አልተነደፈም፡፡

በአጠቃላይ ከተገኘው የመረጃ ትንተና ውጤት መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ንግግርን ሲያስተምሩ ሙሉ በሙሉ መሰረት የሚያደርጉት የተማሪውን የመማሪያ መፅሐፍ መሆኑ እና የሚቀርቡት የመነጋገሪያ ይዘቶች የተማሪዎቹን ትምህርት ደረጃ አለመገምገማቸው እንዲሁም የእለቱን ትምህርት ፣ዓላማና መመሪያ ማስተዋወቅ በሚመለከት በምልከታ፣በጽሁፍና በቃለ መጠይቅም የተገኘው መረጃ መካከለኛ እንደሆነ አመላክቷል፡፡እንዲሁም በቅድመ መናገር ተግባራት ክንውን ጊዜ የእለቱ ትምህርት ከመቅረቡ በፊት የተማሪዎችን የመናገር ፍላጎት ለማነሳሳት የተለያዩ የማነቃቂያ ብልሃቶችን ሲጠቀሙ ብዙም አለመታየታቸው ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ እና ከምልከታው ከተገኘው ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 4.4. በክፍል ውስጥ በሚቀርበው የመናገር ትምህርት ልምምድ ጊዜ የመምህሩ ተግባር

እንደ (scrivener, 1994,59) አገላለጽ "በቋንቋ ክፍል ውስጥ ለሚደረገው ንግግር በርካታ ተግባራት ቢኖሩም ዋናው አላማ ለንግግር የልምምድ እድል መስጠት ነው" ይላሉ፡፡ስለዚህም መምህሩ ተማሪዎች የንግግር ልምምድ በሚያደረጉበት ጊዜ መከታተል፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መርዳትና ማበረታታት ይጠበቅበታል፡፡የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃውና ትንታኔው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ5፡-በተማሪዎች የክፍል ውስጥ የመናገር ትምህርት ልምምድ ጊዜ የመምህሩ ተግባርን በተመለከተ በምልከታ የተገኘ ውጤትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የምልከታ መከታተያ ነጥቦች | የምልከታውአማራጮች በቁጥር እና በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ/ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | |
| | | በቁ | በ% | በቁ | በ% | በቁ | በ % | በቁ. | በ% |
| 6 | ተማሪዎች በጥንድ ወደ ልምምድ ተግባር እንዲገቡ ያደርጋል፡፡ | 3 | 75 | | | 1 | 25 | | |
| 7 | በመናገር ልምምዱ ጊዜ ሁሉንም ተማሪዎች እንዲናገሩ ያሳትፋል፡፡ | | | | | 3 | 75 | 1 | 25 |
| 8 | በልምምድ ጊዜ ፍረሃት ወይም ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን ያበረታታል፡፡ | | | | | 3 | 75 | 1 | 25 |
| 9 | መምህሩ/ሯ/የመናገር ክሂልን በማለማመድ ጊዜ የተጠቀሟቸው ይዘቶች:- | | | | | | | | |
| | ውይይት | | | 2 | 50 | | | | |
| | ጭውውት | | | 1 | 25 | | | | |
| | ክርክር | | | 1 | 25 | | | | |

ከሰንጠረዥ አመስት መረዳት እንደሚቻለው በክፍል ውስጥ ንግግርን በመማር ማስተማር ሂደት መምህሩ ተማሪዎችን ወደ ልምምድ እንዲገቡ የማድረጉ ሁኔታ ምን ያህል ነው? ለሚለው ጥያቄ 3(75%)የሚሆኑት መምህራን ተማሪዎች ወደ ልምምድ ተግባር እንዲገቡ የማድረግ ሁኔታ‹‹በጣም ከፍተኛ ›› ሲሆን 1(25%) ያህሉ መምህራን ደግሞ ‹‹መካከለኛ››የሆነ ጥረት ሲያደርጉ በምልከታው ለመረዳት ተችሏል፡፡

ይህን አስመልክቶ (Ur,1996,25) ሲገልፁ “መምህሩ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለንግግር የተመደበላቸውን ጊዜ ንግግርን በማለማመድ እንጂ ለንግግር የሚሰጠውን ክፍለ ጊዜ ሌላ ተግባር በማሰራት ማሳለፍ የለበትም፡፡ስለሆነም ተማሪዎችን በጥንድ፣ በቡድን እና በግል የሚለማመዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ከሁሉም የቋንቋ መምህራን የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡”በማለት ገልፀዋል፡፡

እንዲሁም(Sahar,2014,4) "የቋንቋ መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ትምህርቱ ሲቀርብ ሚናቸው ተማሪዎች እርስ በርስ መስተጋብር እንዲፈጥሩ ማበረታታት ማለትም የሚፈልጉትን ነገር በራሳቸው አገላለፅ በመጠቀም ሀሳባቸውንየሚገልፁበት ፤የንግግር ችሎታቸውን ለማሳደግ በራስ የመተማመን ስሜታቸውን ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ ጥረት የሚደረግበት ነው፡፡ይህንን ጉዳይ ከግብ ለማድረስ መምህራንየተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን በክፍል ውስጥ መጠቀም ይኖርባቸዋል" በማለት ገልፀዋል፡፡ ሌላው ከሰንጠረዡ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው በምልከታው ወቅት መምህራን ልምምዱ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እናዳይያዝ የማድረግ ሁኔታን በተመለከተ 3(75%) መምህራን‹‹መካከለኛ››ሲሆን 1(25%) ደግሞ‹‹ዝቅተኛ››በሆነ መልኩ ተማሪዎችን ሲያሳትፉ በምልከታው ለማየት ተችሏል፡፡ይህም ከመምህራን የቃለ መጠይቅ ምላሽ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም በዚሁ ሰንጠረዥ በምልከታ መከታተያ መስፈርት ስምንተኛው ላይ ከሰፈረው ምላሽ መረዳት እንደተቻለው 3(75%)ያህሉ መምህራን ‹‹መካከለኛ››በሆነ መልኩ የማበረታታት ስራን ሲከውኑ ታይተዋል፡፡ማለትም ተማሪዎች ንግግር ሲያደርጉ ሲጠፉባቸው ከመቆጣት ይልቅ ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ "ጥሩነው ለሚቀጥለው ጥሩ ልምምድ አድርጋችሁ ንግግር ለማድረግ ሞክሩ አትፍሩ" በማለት ድጋፍ ሲሰጡ ለማየት ተችሏል፡፡ ሌሎቹ 1(25%)ቱ መምህራን ደግሞ ተማሪዎች ሲፈሩ በማበረታታት ፋንታ ቁጭእንዲሉ እና እጅ አውጥተው ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ብቻ በመጠየቅ ልምምዱን በክፍል ውስጥ ሲያካሂዱ ለማየት ተችሏል፡፡በመሆኑም ከመሳተፍ ይልቅ አድማጭብቻ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

መምህራን ለሚያስተምሩት ትምህርት ተማሪዎቻቸውን የሚመጥን ለትምህርት ይዘቶቹ ተስማሚ የሆነ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መምረጥ ይገባቸዋል፡፡ይህን ሀሳብ በተመለከተ (Harmer,2007,129) መምህራን የመናገር ክሂልን በሚያለማምዱበት ጊዜ የተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃቶችን በመጠቀም ሲያለማምዱ በይዘቱና በክንውኑ ላይ ያተኮሩ ተግባራት ሊሆኑ ይገባል፤ከብልሃቶቹም ውስጥ ውይይት፣ክርክር፣ ጭውውት የሚገኙበት ሲሆን ተማሪዎቹ ለሚመጥናቸው ደረጃ የመለማመጃ ክንውኖች መምረጥ ተገቢ ነው፡፡"በማለት ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በክፍል ውስጥ ምልከታ እንደታየው 2(50%) የሚሆኑት መምህራን በክፍል ውስጥ ውይይት ሲያካሂድ 1(25%) የሚሆኑት ደግሞ ባህላዊ ጭውውት ተለማምደው በክፍል ውስጥ

ሲያቀርቡ እንዲሁም 1(25%) ያህሉ መምህራን ክርክርን ለንግግር ክሂል ትምህርት ማለማመጃነት ሲጠቀሙ በምልከታው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡-የመምህራን የማለማመድ ክንውኖችን በተመለከተ የመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ**

| ተ.ቁ | ዝርዝርጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አብዛኛውንጊዜ | | አንዳንድጊዜ | | በፍፁም | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 4 | ለመናገርየማይደፍሩናሀሳባቸውንበንግግርለመግለፅየሚቸገሩተማሪዎችን በነጻነት እንዲናገሩ አበረታታለሁ፡፡ | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 50 | | |
| 5 | የንግግርማስተማሪያብልሃትን(ጭውውትን) በመጠቀምሀሳባቸውን በንግግር እንዲገልፁአደርጋለሁ፡፡ | | | 3 | 75 | 1 | 25 | | |

ከላይ በሰንጠረዥ ስድስት እንደሚታየው የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል 1(25%) ‹‹ሁልጊዜ›› በነጻነት እንዲናገሩ አበረታታለሁ ሲሉ 1(25%)1ቱ ደግሞ ‹‹አብዛኛውን ጊዜ›› በነጻነት እንዲናገሩ አበረታታለሁ በማለት ምላሽ ሲሰጡ እንዲሁም ደግሞ 2(50%) ‹‹አንዳንድ ጊዜ›› ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸውን ለመግለፅ የሚቸገሩ ተማሪዎች በነጻነት አበረታታለሁ ማለታቸውን ከፅሁፍ መጠይቁ ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡ከምላሹ መገንዘብ የሚቻለው ሁሉም መምህራን ለመናገር የማይደፍሩትን ተማሪዎች የማበረታታቱ ሁኔታ በተወሰነ መልኩየተሻለ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

እንዲሁም ደግሞየጽሑፍ መጠይቁን ለሞሉት መምህራን ቃለ መጠይቅም ተደርጎላቸዋል፡፡ጥያቄውም ‹‹ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር እንዳይገልፁ የሚያደርጉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ምንምን ናቸው?›› ለሚለው የተለያዩ ምክንያቶችን ሰንዝረዋል፡፡ መታቀብ ይኸውም አብዛኞቹ ተማሪዎች ከገጠር አካባቢዎች ስለሚመጡ እና አሁን የሚማሩበት ትምህርት ቤት ለእነሱ አዲስበመሆኑ ከተማሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡በዚህ ጊዜ በክፍል ውስጥ ንግግርን ለመለማመድ ድፍረት ማጣት፣ንግግር ባደርግ ይስቁብኛል፣ትክክለኛ ባልሆንስ የሚሉ አመለካከቶች በውስጣቸው ስላለና በራስ የመተማመን ስሜት አለመኖር፣ለትምህርቱ ትኩረት አለመስጠት እንዲሁም አካባቢያዊ ባህላቸው በተለይ ሴቶች ላይ ‹‹ዝምታ ወርቅ ነው›› የሚለውን ሀሳብ የሚያበረታታ በመሆኑ ሀሳባቸውን በንግግር እንዳይገልፁ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድርጎባቸዋል፡፡እንዲሁም ደግሞ ተማሪዎች የመናገር ፍላጎት እያላቸው አንዳንድ ጊዜ ለንግግር ስለቀረበው ጉዳይ በቂ መረጃ ስለማይኖራቸው ለመናገር አይደፍሩም፡፡ይህም የሚሆንበት ምክንያት ለንገግገር የተመረጠው ርዕስ የተማሪዎችን ደረጃ፣ፍላጎትትና የትምህትት ደረጃ ያላገናዘበ ከሆነ ተማሪዎቹ እንዳይሳተፉ ያደርጋቸዋል፡፡ይህም ተማሪዎች የሚናገሩትን ነገር ያሳጣል በማለት ሲመልሱ ከዚህ ጥያቄ ጋር የተያያዘ ሌላ ጥያቄም ተጠይቀዋል፡፡ጥያቄውም ‹‹ለችግሮቹ መፍትሄ ምንድነው ይላሉ?›› ለሚለው እያንዳንዳቸው መምህራን የየራሳቸውን ሀሳብ በመፍትሄነት አቅርበዋል፡፡ 3(75%) ያህሉ መምህራን ለእንደነዚህ አይነት ተማሪዎች፣ንግግር የሚያደርጉበትን አጋጣሚ መፍጠር፣ፍርሃት ያለባቸውን ተማሪዎች በቡድን ውይይት ጊዜ የተወያዩበትን ሀሳብ በንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ለንግግር ትምህርት ትኩረት እንዲሰጡ ማነሳሳት፣ ሲሳሳቱ ሳይቆጡ አዎንታዊ በሆነ መልኩ ማበረታታት፣ከማያውቁት ይልቅ የሚያውቁትን ነገር

ተለማምደው ንግግር እንዲያደርጉ ማበረታታት እና ከአካባቢያቸው ጋር የተገናዘበ ይዘት ማስመረጥና እንዲናገሩ ማድረግ በመፍትሄነት ጠቁመዋል፡፡1(25%)ቱ መምህራን ደግሞ የተማሪዎችን ፍርሃት ለማስወገድ እና የማይተዋወቁ ተማሪዎችን እርስ በራሳቸው እንዲግባቡ ለማድረግ የቡድን ስራ መስጠት እና አብረው ሰርተው ንግግር እንዲያደርጉ ማበረታታት እንደመፍትሄ ሊሆን ይችላል በማለት ሀሳባቸውን ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የተለያዩ ተግባራትን (ክርክርን እና ጭውውትን ) በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረጋቸውን ከክፍል ውስጥ ምልከታው፣ከፅሁፍ መጠይቁና ከቃለ መጠይቁ ምላሽ ጋር የተገናዘበ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ7፡-**በልምምድ ደረጃ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በሚመለከት የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝርጥያቄዎቸ | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 5 | መምህሩ/ሯ/ ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎችን በነፃነት እንዲናገሩ የማበረታታት ሁኔታ እንዴት ይገለፃል ? | 100 | 31.1 | 200 | 62.1 | 22 | 6.8 | | |
| 6 | መምህሩ/ሯ/በጥንድ ወይም በቡድን እንድትወያዩና እንድትለማመዱ የሚያደርጉት ጥረት እንዴት ይገለፃል | 100 | 31.1 | 72 | 22.3 | 150 | 46.6 | | |

ከላይ ከሰንጠረዥ ሰባት መረዳት እንደሚቻለው ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎችን መምህራን እንዲናገሩ የማበረታታቱ ሁኔታ እንዴት እንደሆነ ለመገምገም ለቀረበላቸው

ጥያቄ 100(31.1%) የሚሆኑት ተማሪዎች‹‹ሁል ጊዜ ያበረታቱናል››በማለት ምላሽሲሰጡ 200(62.1%)ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ በልምምድ ጊዜ የሚፈሩ ተማሪዎችን የማበረታታቱ ሁኔታ ‹‹አብዛኛውን ያበረታቱናል›› በማለት ምላሽ የሰጡ ሲሆን 22(6.8%)የሚሆኑት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ‹‹አንዳንድ ጊዜ ያበረታቱናል›› በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡በአጠቃላይ ከምላሻቸው መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች የልምምድ ተግባራትን ሲያከናውኑ ፍረሃት ያለባቸውን ተማሪዎች የማበረታታት ሁኔታ የተሻለ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ከዚህ ሃሳብ ጋር በዚሁ ሰንጠረዥ ጥያቄ ቁጥር ስድስት መምህራን በጥንድ ወይም በቡድን እንድትወያና እንድትለማመዱ የሚያደርጉት ጥረት እንዴት ይገለፃል ?ለሚለው ጥያቄ 100(31.1%)ያህሉ ተማሪዎች“ሁል ጊዜ እንድንለማመድ ያደርጉናል”በማለት ምላሽ ሲሰጡ 72(22.3%)ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ“አብዛኛውን ጊዜ እንድንለማመድ ያደርጉናል”ሲሉ 150(46.6%)ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ “አንዳንድ ጊዜ እንደንለማመድ ያደርጉናል” በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ይህም ምላሽ በክፍል ውስጥ ከተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡ምክንያቱም በምልከታ ወቅት 3(75%) መምህራን ተማሪዎችን ለማሳተፍ እና እንዲናገሩ ለማድረግ “መካከለኛ” የሆነ ጥረት ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡ በተቃራኒው 1(25%) የሚሆኑት ደግሞ ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲገልፁበቂ የማለማመጃ ጊዜ አለመሰጠት እና ለሚለማመዱበት ይዘት ግልጽ መመሪያ አለመስጠት የተማሪዎች የንግግር ክሂል በሚፈለገው ደረጃ እንዳይደርስ አድርጎታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተተነተነው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራትን እንዲለማመዱ፣የተሰጡትን ተግባር በተሰጣቸው ጊዜ ተለማምደው በተቻለ መጠን ራሳቸውን ችለው እንዲያቀርቡ ማነሳሳት፣ፍረሀት ያለባቸውን ተማሪዎች የማበረታታት እና ክሂሉን ለማለማመድ መምህራኑ የተጠቀሟቸው የማስተማሪያ ብልሃቶች በተወሰነ መልኩ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ጥረት የተደረገ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ፣ የመምህራን ቃለመጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ይህንኑ ሃሳብ የሚያጠናክር ናቸው፡፡፡

ይህን ሀሳብ በተመለከተ (Ricards and Nunan, 1991,15)እንዳብራሩትሰ“የማስተማሪያ ብለሃት ማለት የተመረጠውን የትምህርት ይዘት በቅደም ተከተል ለተማሪዎች የምናቀርብበት መንገድ ወይም ስልት ሲሆን የማስተማሪያ ብልሃቱ ሲመረጥም

የትምህርቱ ይዘት፣የተማሪዎቹ ዳራዊ እውቀት እና ከትምህርቱ በኋላ ልናሳካው የምንጠብቀውን የመማር ውጤት መሰረት የሚያደርግ መሆን ይገበዋል"በማለት ገልፀዋል፡፡ስለሆነም መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ በልምምድ ደረጃ መከናወን ያለባቸው ሂደቶች በተገቢው ሁኔታ ማቅረብ እንዳለባቸው ልብ ሊሉት ይገባል፡፡ምክንያቱም ተማሪዎች ወደ አፍልቆት ደረጃ ከመሸጋገራቸው በፊት በክፍል ውስጥ በግል፣በጥንድ፣በቡድን በቂ ልምምድ ማድረግና ክንውኑ የመምህራንን ክትትልና ድጋፍ በሚመለከተው ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ቢሰጡም በክፍል ውስጥ ምልከታው መረዳት እንደተቻለው ግን አብዛኞቹ መምህራን እነዚህን ተግባራት ብዙም ሲተገብሩት አልታዩም፡፡

## 4.5 የአፍልቆት ደረጃ ክንውኖች የመረጃ ትንተና

የአፍልቆት ደረጃ ተግባራት ማለት ተማሪዎች ከመምህራን ትእዛዝ ነፃ ሆነው በራሳቸው አገላለጽ ሀሳባቸውን ለሌላ አካል በንግግር ለመግለጽ የሚጥሩበት ነው፡፡እንደ (Harmer, 1991, 50) አገላለጽ "ይህ ደረጃ መምህሩ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ የሚረዱ ተግባራትን በመስጠት የመምራትና የማማከር ሚናን የሚጫወቱበት ሂደት ነው፡፡"በማለት አስረድተዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 8፡-** የመምህራንን የአፍልቆት ደረጃ ክንውኖች በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘ ውጤትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የምልከታ መከታተያ ነጥቦች | የምልከታው አማራጮች በቁጥር እና በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ/ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 11 | በአፍልቆት ወቅት ተማሪዎችን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ያበረታታል፡፡ | | | 3 | 75 | | | 1 | 25 |
| 12 | አፍልቆቱበተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ ያደርጋል፡፡ | | | | | 3 | 75 | 1 | 25 |
| 13 | የመናገር ክሂል ተምህርት ይዘቱ | | | | | 1 | 25 | 3 | 75 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ተማሪዎችን በቀላሉና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል አውድ ይፈጥራል፡፡ | | | | | | | | |
| 14 | ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ሃሳብ እንዲሰጡ ያበረታታል ፡፡ | | | 4 | 100 | | | | |
| 15 | ተማሪዎችን እርስ በእርሳቸው የሚነጋገሩበት እድል ይፈጥራል፡፡ | | | | | 3 | 75 | 1 | 25 |

ከሰንጠረዥ ስምንት ከምልከታ መከታተያ ነጥብ አስራ አንድ ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ከአንድ መምህር በስተቀር ሌሎቹ መምህራን በተማሪዎች የንግግር አፍልቆት ጊዜ ጣልቃ በመግባትና ንግግርን እንዴት ሊያከናውኑ እንደሚችሉ ማብራሪያ በመስጠት ላይ ያተኮሩ እንደነበር መመልከት ተችሏል፡፡ በተለይ አንደኛዋ መምህርት ተማሪዎች ጭውውት ሲያደርጉ በጭውውቱ ጊዜ አንዳንድ አነጋገር ሲሳሳቱ በማስቆም አስተያየት ሰጥተው ደግሞ ጭውውቱ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ አንዱ መምህር ግን ለየት ያለ አቀራረብንአሳይቷል፡፡ ይኸውም የተለማመዱትን ይዘት ከማቅረባቸው በፊት ስለአቀራረቡ ማብራሪያ ሰጥቶ የተለማመዱትን ያለ መምህሩ ጣልቃ ገብነት እንዲያከናውኑ አድርጓል፡፡በመጨረሻም ተማሪዎች በቀረበው የንግግር ይዘት ያላቸውን አስተያየት፣ ከንግግሩ ምን ጠቀሜታ እንዳገኙ፣አስተያየት እንዲሰጡ ጥረት አድርጓል፡፡

ይህንሃሳብ አስመልክተው (Byrne,1987) እንዳብራሩት "ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ መምህሩ ጣልቃ በመግባት ማስቆም የለበትም፡፡ ምክንያቱም ጣልቃ በመግባት እርማት ለመስጠት መሞከር ቀጣይ የሆነውን የመማር ማስተማር ተግባር እንደ መግታት የሚቆጠር በመሆኑ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ አላስፈላጊ እርማት በመስጠት ተማሪዎችን ማሸማቀቅ የለበትም፡፡ ማረሙ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ እንኳን ተማሪዎች በቀጥታ በማያውቁት መልኩ የራሳቸውን የተለየ ስልት ተጠቅመው ማስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡"በማለት ገልፀዋል፡፡

ይህን ሃሳብ በተመለከተ (Ur,1996) "የክፍል ውስጥ ልምምድ በጥቂት ተማሪዎች ተፅዕኖ ስር ብቻ መውደቅ የለበትም፡፡ ስለሆነም ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች የመናገር እድል ሊሰጣቸውና ተሳትፏቸው ተቀራራቢና የተመጣጠነ ሊሆን ይገባል፡፡" በማለትገልፀዋል፡፡ የምሁሩን/ሯ/ን ሃሳብ መሰረት በማድረግ በዚህ ጥናት ወቅት የተደረገው የምልከታ ውጤትም ሲታይ 3(75%) የሚሆኑት መምህራን "መካከለኛ" የሆነ የአፍልቆት እድል ሲሰጡ ሌሎቹ 1(25%) መምህራን ደግሞ"ዝቅተኛ"የሆነ የአፍልቆት እድል ሰጥተዋል፡፡ ይኸውም በተሰጣቸው የንግግር ይዘት ንግግሩን የሚያደርጉት ተማሪዎች ደግሞ ሁሉም አልነበሩም፤ እጅ ያወጡትን ተማሪዎች ብቻ በመጠየቅ ንግግር እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡ስለሆነም ሁሉም ተማሪዎች እኩል የተሳትፎ እድል አላገኙም፡፡ በመሆኑም ፍርሃት ያለባቸውን ተማሪዎች የማበረታታትና እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማድረጉ ሁኔታ መካከለኛ እንደነበረ መመልከት ተችሏል፡፡

እንዲሁም መምህሩ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ የሚረዱ ተግባራትን በመስጠት የመምራትና የማማከር ሚናን መጫወት ይኖርበታል፡፡ በአፍልቆት ደረጃ ዋናው ትኩረት ተማሪዎች በቀላሉና በነፃነት የሚግባቡበትን አውድ መፍጠር እና በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው በማለት(Harmer, 1991)ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በክፍል ውስጥ ከተደረገው ምልከታ 1(25%) ቱ መምህራን ብቻ "መካከለኛ" በሚባል ደረጃ ተግባራዊ ሲያደርጉ ለማየት ተችሏል፡፡ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ተጠቅመው የተሰጣቸውን ተግባር "ባህላዊ ጭውውት" በራሳቸው መንገድ በነፃነትና ሁሉንም ሊያግባባ በሚችል አውድ በተቀራረጠ መንገድም ቢሆን ሃሳባቸውን የሚገልፁበትን ሁኔታ ሲያመቻቹ ተስተውለዋል፡፡ ሌሎች መምህራን 3(75%)ግን በአብዛኛው ተማሪዎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነበር፡፡ ሁሉም መምህራን ተግባሩን ይሰጣሉ ግን ተግባሩ ውስብስብ እንዲሁም በቀላሉ ሊያወያይ የሚችል ሆኖ ሳለ ለመለማመጃ የሚሰጧቸው ጊዜ አጭር በመሆኑ ቶሎ የገባቸው ንግግር ሲያደርጉ ሌሎች ግን በፍርሃት አለመናገርን ሲመርጡ ታይቷል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ተግባሩን በፈቀዱት እና በሚገባቸው መልኩ ግልጽ የሆነ መመሪያ በመስጠት ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ የማድረጉ ሁኔታ ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል፡፡ .

እንደ (Harmer,2007) አገላለፅ የቡድን ስራ ማለት ተማሪዎች ሁለት እና ከዚያ በላይ ሆነው የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ከሌሎች መሰል ጓደኞቻቸው ጋር በቡድን ሲሰሩ የመመራመር ችሎታቸውያሻሽላል፤ሃሳባቸውን

ከነባራዊ እውነታ ጋር በማዛመድ እንዲናገሩ ያደርጋል በማለት ይገልፃሉ፡፡ ከምልከታው የተገኘውም ውጤት አራቱም መምህራን ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ልምምድ እንዲያደርጉ የማበረታታቱ ሁኔታ "ከፍተኛ" መሆኑን አሳይቷል፡፡

ይሁን እንጂ በቡድን የተወያዩበትን ሃሳብ ጽብረቃ እንዲያካሂዱ የማበረታታቱ ሁኔታ "ዝቅተኛ" እንደነበረ ለመመልከት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ምልከታ የተደረገበት ሌላውመስፈርት ደግሞ ተማሪዎች ያለማንም ጣልቃገብነት እርስ በራሳቸው የሚነጋገሩበት እድል የመስጠቱ ሁኔታ ጥሩ ሆኖ በጥንድ ወይም በቡድን የሚሰሩትን ለክፍሉ ተማሪዎች ሪፖርት የማቅረቡ ሁኔታ 3(75%) የሚሆኑት መምህራን ተማሪዎች እንዲያቀርቡሲያደርጉ ለመመልከት ተችሏል፡፡ 1(25%)የሚሆኑት መምህራን ግን በባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለምን እንደተወያዩ ርዕሱን በመጠየቅ ራሳቸው መምህሩ ማብራሪያ ሰጥተው በባለፈው ክፍለ ጊዜ በተሰጡት የመወያያ ርዕስ ዙሪያ ያልገባቸው ካለ እንዲጠይቁ እድል ከመስጠት ውጪ የተገበሩት ምንም አይነት ተግባር አልነበረም፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ባቀረቡት ሪፖርት ላይ አስተያየት የመስጠቱ ሁኔታ ሲታይ አንድ መምህር ብቻ ፍርሃታቸውን የሃሳብ መቆራረጥ እና የቃላት አጠቃቀም ችግር መኖሩን ሲገልፁ ሌሎች መምህራን ግን ምንም አይነት አስተያየት አልሰጡም፤ ተማሪዎችም በቀረበው ሪፖርት ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አልተደረጉም፡፡

**ሠንጠረዥ** 9፡- በአፍልቆት ደረጃ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በሚመለከት የመምህራንን የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ዝርዝርጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | በፍፁም | |
| | | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % |
| 6 | የመናገር ክሂል ትምህርት አፍልቆትበተወሰኑተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን እቀይሳለሁ፡፡ | 1 | 25 | 3 | 75 | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ለመናገር የማይደፍሩና ሃሳባቸዉን በንግግር ለመግለፅ የሚቸገሩ ተማሪዎችን በነጻነት እንዲናገሩ አበረታታለሁ፡፡ | | | 3 | 75 | 1 | 25 | | |

ከላይ ከሰንጠረዥ ዘጠኝ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የመናገር ክሂል ትምህርት አፍልቆቱ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ የተለያዩ የማስተማር ስልቶችን መቀየስን በተመለከተ "ሁልጊዜ" የራሴን ስልት እቀይሳለሁ ያሉት መምህራን 1(25%) ያህሉ ሲሆኑ 3(75%)ቱ መምህራን ደግሞ "አብዛኛውን ጊዜ" የተለያዩ የማስተማር ስልቶችን እቀይሳለሁ በማለትምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ምላሽ ከምልከታው ውጤት ጋር ሲነፃፀር ብዙም የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነምመምህራኑ በጽሁፍ ከሰጡት ምላሽ ይልቅ በምልከታ የታየውአስተማማኝ በሆነ መልኩ የመምህራኑን ክንውን በግልፅ አመላክቷል፡፡

በመቀጠል በጥያቄ ቁጥር ሰባት የቀረበው ለመናገር የማይደፍሩና ሃሳባቸዉን በንግግር ለመግለፅ የሚቸገሩ ተማሪዎችን በነፃነት እንዲናገሩ ማበረታታት የሚል ሲሆን የፅሁፍ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን 3(75%) ያህሉ "አብዛኛውን ጊዜ" እንዲናገሩ አበረታታለሁ የሚለውን ምላሽ ሲሰጡ 1(25%)ቱ መምህራን ግን "አንዳንድ ጊዜ" እንዲናገሩ አበረታታለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ይህ የፅሁፍ ምላሽ በክፍል ውስጥ ከተደረገው ምልከታ ጋር ሲነፃፀር ተቃራኒ ሆኖተገኝቷል፡፡ይኸውም በክፍል ውስጥ ምልከታው እንደታየው ተማሪዎች ንግግራቸውን ሲያቀርቡ ስህተት ሲፈፅሙ የማሸማቀቅ፣ በመካከል ጣልቃ በመግባት ማስተካከያ የመስጠት እና የማበረታቻ ቃላትን ሲነፍጉ ታይተዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በነፃነት ከመግለጽ ይልቅ ዝምታን ሲመርጡ ለማየት ተችሏል፡፡ ስለሆነም ከጽሁፍ መጠይቁ ከተሰጠው ምላሽ ይልቅ ተአማኒነት ያለው በተግባር ሲያከናውኑ በምልከታ የታየው በመሆኑ መምህራኑ ከሰጡት የጽሁፍ መጠይቅ በአይን የታየውን የምልከታ ውጤት እውነታ ያለው እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ** 10፡- በአፍልቆት ደረጃ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በሚመለከት የተማሪዎችን የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % | በቁጥር | በ % |
| 7 | የመምህሩ/ሯ/ የመናገር ክሂል ትምህርት በሚያስተምሩበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የተሳትፎ እድል የመስጠቱ ሁኔታ እንዴት ይገለፃል? | 100 | 31.1 | | | 200 | 62.1 | 22 | 6.8 |
| 8 | መምህሩ/ሯ/የመናገር ክሂላችሁን ለማሳደግ በጥንድ ወይም በቡድን በማደራጀት ጭውውት እንድታቀርቡ የሚያደርጉት እንዴት ነው? | | | | | 290 | 90.1 | 32 | 9.9 |

ከላይ በሰንጠረዥ አስር እንደተገለፀው ሰባተኛው ጥያቄ በመናገር ክሂል ትምህርት ሂደት መምህራን በክፍል ውስጥ ትግበራ ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የተሳትፎ እድል የመስጠቱ ሁኔታ ሲሆን100(31.1%)ያህሉ ተማሪዎች "ሁልጊዜ" እኩል የተሳትፎ እድል እንደሚሰጧቸው ምላሽ ሲሰጡ200(62.1%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ መምህራኑ የተሳትፎ እድል የሚሰጧቸው "አንዳንድ ጊዜ"እንደሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡እንዲሁም 22(6.8%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ "በፍፁም የተሳትፎ እድል አይሰጡንም" የሚለውን መልስ በመምረጥ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ይህም ምላሽ የሚያስረዳው አብዛኛዎቹ መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን በሚያስተምሩበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የተሳትፎ ዕድል እንደማይሰጡ ነው፣ይህም አብዛኞቹ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳትፉት እጃቸውን ለሚያወጡ ተማሪዎች እንጂ ሁሉንም አይደለም፡፡ይህንንም ሀሳብ በክፍል ውስጥ

ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ስለሆነም ይህ ሃሳብ ከክፍል ውስጥ ምልከታው መረጃ ውጤት ጋር ተመሳሳይነትና ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

እንዲሁም በዚሁ ሰንጠረዥ ውስጥ ለሚገኘው ለስምንተኛው ጥያቄ290(90.1%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን በማደራጀት ጭውውት "አንዳንድ ጊዜ"እንደሚያቀርቡ ምላሽ ሲሰጡ 32(9.9%) የሚሆኑትተማሪዎች ግን "ምንም ነገር አቅርበው እንደማያውቁ" ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም ምላሽ የሚያስረዳው አብዛኛዎቹ መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ በጥንድ ወይም በቡድን በማደራጀት ጭውውት እንዲያካሂዱ የማድረጉ ሁኔታ "ዝቅተኛ" መሆኑን ያመላክታል፡፡ይህም ውጤት ከክፍል ውስጥ ምልከታው ጋር የሚዛመድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 4.6. የመናገር ክሂል ትምህርት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ክንውኖች ትንተና

እንደ Gower *et .al.* (1995:163) አገላለፅ ምጋቤ ምላሽ ተማሪዎች የሰሩትን ሥራ ጥንካሬና ድክመትን ማመላከቻ በመሆኑ ጥሩው እንዲቀጥል ድክመቱ እንዲሻሻል እድል ይሰጣል፡፡ የተማሪዎችንም ስኬት የመምህሩንም የማስተማሪያ ብልሃት እንዲገመግም መንገድ ያሳያል፡፡ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ የተለያዩ መንገዶችን የሚከተል ሲሆን ምስጋናና ማበረታቻ እንዲሁም እርማት መስጠት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በመናገር ክሂል አተገባበር የምጋቤ ምላሽ እንዴት በክፍል ውስጥ እንደተከናወነ ማየት ይቻል ዘንድ በምልከታ የታየውን የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ለማብራራት ተችላል፡፡

ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ የድህረ ንግግር አንዱ ተግባር ሲሆን ተማሪዎች በተሰጣቸው ወይም በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ምን ያህል ተጠየቃዊ ሀሳብን እንዳብራሩበት የሚገመገምበት ሂደት ነው፡፡ስለሆነም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ተማሪዎች ንግግርን ሲያደርጉ የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ወደፊት ስህተቱን እንዳይደግሙት የማድረጊያ ስልት ነው፡፡በክፍል ውስጥ ምልከታው የታየውን የመምህራን ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ አሰጣጥ ሂደት በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ11፡-የመምህራንን በክፍውስጥቃላዊምጋቢምላሽአሰጣጥበምልከታ የተገኘው ውጤትየሚያሳይሰንጠረዥ

| ተ ቁ. | የምልከታ መከታተያ ነጥቦች | የምልከታው አማራጮች በቁጥርና በመቶኛ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ/ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 17 | የመምህራን በመናገር ክሂል ትምህርት ወቅት ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ የመስጠት ሁኔታ | | | | | | | | |
| | 17.1 ንግግሩን ያቀረበው/ችው/ ተማሪ ስህተቱን እንዲያይ/እንድታይ/ እና እንዲናገር/እንድትናገር/ ማበረታታት | | | | | | | 4 | 100 |
| | 17.2 ሌሎች የክፍሉ ተማሪዎች የተማሪው/ዋ/ን ስህተት እንዲናገሩ ማድረግ | | | | | | | 4 | 100 |
| | 17.3ተማሪዋ/ው/ የሰራውን/ችውን ስህተት ራሱ/ሷ/ንማረም | | | | | 3 | 75 | 1 | 25 |

እንደ Fayzah (2012:6) አገላለፅ "ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ከድክመት ይልቅ ጥንካሬን መነሻ በማድረግ መስጠት በእርማት አሰጣጥ ደግሞ ለተማሪው ለእራሱ ቅድሚያ በመስጠት ስህተቱን እንዲናገር የሚደረግበት ሲሆን ተማሪው ካልተረዳው ሌሎች የክፍል ጓደኞቹና መምህሩ ስህተቱን የሚጠቁሙበት ሂደት ነው፡፡"በማለት አስረድተዋል፡፡ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት የመምህራን የቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ ሲታይ ንግግሩን ያቀረበው/ችው/ ተማሪ ስህተቱን/ቷን/እንዲያይ/ታይ/ እንዲናገር/እንድትናገር/የማበረታታቸው ሁኔታ 4(100%) "ዝቅተኛ"እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ሌሎች የክፍሉ ተማሪዎች ንግግሩን ያቀረበውን ተማሪ ስህተት እንዲናገሩ ከማድረግ አኳያም እንዲሁ "ዝቅተኛ" እንደነበር ለማየት ተችሏል፡፡ሌላው ከዚሁ ሃሳብ ጋር የተያያዘ ጥያቄ እንዲሁም ሌሎች የክፍሉ ተማሪዎች ንግግሩን ያቀረበውን ተማሪ ስህተት እንዲናገሩ ከማድረግ አኳያም እንዲሁ "ዝቅተኛ" እንደነበር ለማየት ተችሏል፡፡ሲታይ75%የሚሆኑት መምህራን

“መካከለኛ”በሆነመልኩ የማረም ሁኔታ እንዳለ ለማየት ተችሏል፡፡25%ቱ መምህራን ደግሞ የተማሪዎችን ስህተት ራሳቸው ተማሪዎቹ ከማረም አንጻር ያላቸው እንቅስቃሴ“ዝቅተኛ” መሆኑን መመልከት ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 12 ፡-** በክፍል ውስጥ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተየመምህራንን የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽየሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | በፍፁም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 10 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር ሲያደርጉ ለፈፀሙት ስህተት ወዲያው እርማት እሰጣለሁ፡፡ | | | 1 | 25 | 3 | 75 | | |

ከላይ ከሰንጠረዥ አስራ ሁለት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር ሲያደርጉ ለፈጸሙት ስህተት ወዲያው እርማት የመስጠትን ሁኔታ ተጠይቀው 25%የሚሆኑት መምህራን “አብዛኛው ጊዜ” ወዲያው እርማት እሰጣለሁ፡ ፡ በማለት ምላሽ ሲሰጡ 75%ቱ መምህራን ደግሞ “አንዳንድ ጊዜ”በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡መምህራኑ የሰጡት ምላሽ እና የምልከታው ውጤት ብዙም እንደማይቀራረብ መመልከት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ምንም እንኳን መምህራን የየራሳቸውን የፅሁፍ ምላሽ ቢሰጡም ከእነሱ ምላሽ ይልቅ በምልከታ የታየው በዋናነት እውነታን የያዘ በመሆኑ ተአማኒነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለዚህ በመናገር ክሂል ትምህርት ወቅትየምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ በጣም ደካማና ብዙም ያልተከናወነ ተግባር እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 13 ፡- በክፍል ውስጥ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት የተማሪዎችን የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በሰ% |
| 12 | በክፍልውስጥ ክርክር፣ ውይይት፣ ጭውውት ካቀረባችሁ በኋላ መምህራን ስህተቶቻችሁን የሚያርሟችሁ መቼ ነው? | 12 | 3.7 | 150 | 46.6 | - | - | 160 | 49.7 |

ከላይ ከሰንጠረዥ አስራ ሶስት ከተማሪዎቹ ምላሽ መረዳት የሚቻለው 12(3.7%) የሚሆኑት ተማሪዎች ባቀረብነው ንግግር ማለትም ጭውውት፣ ክርክር፣ ውይይት አቅርበን ምጋቤ ምላሽ ከመምህራን "ወዲያው" እርማት ይሰጠናልየሚል ምላሽ ሲሰጡ 150(46.6%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ "በማግስቱ" እርማትይሰጠናል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡እንዲሁም 160(49.7%) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ በንግግር ወቅት ስህተት ሲፈጽሙ እርማት "በፍፁም እንደማይሰጧቸው" ከሰጡት የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ Fayzah (2012:6) እንደገለፁት "የቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ከድክመት ይልቅ ጥንካሬን መነሻ በማድረግ መስጠት በእርማት አሰጣጥ ደግሞ ለተማሪው ለራሱ ቅድሚያ በመስጠት ስህተቱን እንዲናገር የሚደረግበት ሲሆን ተማሪው ካልተረዳው ሌሎች የክፍል ጓደኞቹና መምህሩ ስህተቱን የሚጠቁሙበት ሂደት ቢሆን ጥሩ ነው፡፡"በማለት አብራርተዋል፡፡ይሁን እንጂ ከተማሪዎቹ የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ መረዳት የሚቻለው በክፍል ውስጥ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 4.7. የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ

በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተለፀዉ ይህ ጥናት የተካሄደዉ ለአራቱ የምርምር ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ነዉ፡፡ ስለሆነም በተደረገዉ ጥናት አራቱም ጥያቂዎች ምላሽ አግኝተዋል፤ የተገኘዉም ከሰነድ ፍተሻ፣ከመምህራን ና ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ እንዲሁም ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ የመረጃ ዉጤቶችን መሰረት በማድረግ ነዉ፤ በተገኘዉ የመረጃ ዉጤት ትንተና መሰረት የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀዉ የዚህ ጥናት ቁልፍ ጥያቂዎች ጥናቱ ሊመልሳቸዉ የሚገባቸዉ የምርምር ጥያቂዎች ሲሆኑ ጥያቂዎቹም በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የመናገር ክሂል ይዘቶችና ተግባራት የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘቡ ናቸዉ? መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የሚረዱ ምን ምን ተግባራትን የጠቀማሉ? የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት መምህራን ምን ምን ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ? መምህራን የመናገር ክሂልን በክፍል ዉስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምንድን ናቸዉ? የሚሉ ጥያቂዎች ናቸዉ፡፡ ለእነዚህ ጥያቂዎች ምላሽ ለማግኘትም የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብን መሰረት ያደረገ የሰነድ ፍተሻ ተከናዉኗል፤ እንዲሁም የመምህራንና የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ፣ የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን ለመከታተል የክፍል ዉስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ እና ለመምህራን የቃለ መጠይቅ ጥያቂዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ስለሆነም በሰነድ ፍተሻ፣ በፅሁፍ መጠይቅ፣ በክፍል ዉስጥ ምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ትንተናዉ ተከናዉኗል፡፡ የጥናቱ ግኝትም በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ዉስጥ የመናገር ክሂል አቀራረብና የክፍል ዉስጥ አተገባበርን በተመለከተ የተለያዩ የጥናት ዉጤት መገኘታቸዉን አመልክቷል፡፡

በመጀመሪያ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ዉስጥ የተካተቱትን የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችንና ተግባራትን አቀራረብን በተመለከተ በዋናነት በሰነድ ፍተሻዉ፣ በመምህራንና በተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሁም በመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንዳመለከቱት አብዛኛዎቹ በመማሪያ መፅሃፍ ዉስጥ የሚገኙት የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ተግባራት በደረጃዉ የሚገኙ ተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘቡ መሆናቸዉን የጥናቱ ግኝት አመልክቷል፡፡ ይህንን ሀሳብ በተመለከተ የመማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁ ማሟላት ከሚገባቸዉ ባህሪያት መካከል የይዘት ተገቢነት አንዱ ሲሆን በደረጃዉ የሚገኙ ተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘቡ መሆን እንዳለባቸዉ በምዕራፍ ሁለት በharmer (1991/257) እና Richard and Rodgers(1986/25) ተገልፃል፡፡ ስለሆነም የጥናቱ ግኝት ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር ተዛማጅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይሁን እንጂ በመማሪያ መፅሃፍት ዉስጥ ያሉት አንዳንድ ይዘቶችና ተግባራት ከተተግባሪነትና ካሳታፊነት አንፃር ዉስንነት ያለባቸዉ መሆኑን የጥናቱ ግኝት አመልክቷል ፡፡

ሁለተኛ የዚህ ጥናት የምርምር ጥያቄ መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የሚረዱ ምን ምን ተግባራትን ይጠቀማሉ? የሚለዉ ሲሆን በክፍል ዉስጥ ምልከታ፣ በመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ፣ እና በመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንዳመለከቱት አብዛኛዎቹ መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ክርክርን፣ ጭዉዉትንና ዉይይትን መጠቀማቸዉን የጥናቱ ግኝት አመልክቷል፡፡ ይህም በምዕራፍ ሁለት ላይ በድሉ(1996፥94-95) ከገለፁት ሀሳብ ጋር ተዛማጅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን የተለያዩ ተግባራት ክርክር፣ ጭዉዉትና ዉይይትን ለማካሄድ የተሰጠዉ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በቂ እንዳልነበረ ክፍል ዉስጥ ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሶስተኛዉ የዚህ ጥናት የምርምር ጥያቄ የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት መምህራን ምን ምን ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ? የሚል ሲሆን በክፍል ዉስጥ ምልከታ፣ በፅሑፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ትንተና እንዳመለከቱት አብዛኛዎቹ መምህራ,ን የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የአመቻችነት፣ ተማሪዎች እርስ በእርስ መተግበር እንዲፈጥሩ የማበረታታትን እና ተማሪዎች ተከታታይ ልምምድ እንዲያደርጉ እድል የመፍጠር ሚናን በሚፈለገዉ ደረጃ ባለመዉጣታቸዉ የተማሪዎች የመናገር ክሂል አንዳንድ ጊዜ የተግባር መሆኑን የጥናቱ ግኝት አመልክቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት መምህራን ከላይ የተገለፁትን ተግባራት ለመወጣት በቂ የመናገር ክሂል ትምህርት ክፍለ ጊዜ ባለመሰጠታቸዉ መሆኑን በሰነድ ፍተሻዉና በምልከታ የተገኘዉ ዉጤት አመልክቷል ፡፡ ይህም ሀሳብ ማረዉ (2003) እና (sahar, 2014) ላይ ከገለፁት ንድፍ ሀሳብ ጋር ተደጋጋፊና ተዛማጅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አራተኛዉ የዚህ ጥናት የምርምር ጥያቄ መምህራን የመናገር ክሂልን በክፍል ዉስጥ በሚተገብሩበት ወቅት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምን ምን ናቸዉ? የሚል ሲሆን በክፍል ዉስጥ ምልከታን በመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ዉጤት እንዳመለከቱት በንግግር ትምህርት ወቅት ከንግግር መታቀብ እና ተማሪዎች የሚናገሩትን ሀሳብ ማጣት በዋናነት ለንግግሩ ትምህርቱ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደሩ ጉዳዮች መሆናቸዉን የጥናቱ  ግኝት አመልክቷል፡፡ የህም ሀሳብ በድሉ (2007፣ 88-89) ላይ ከተገለፁት ንድፈ ሀሳብ ጋር ተዛማጅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ችግር መምህራን በቃል መጠይቁ ተጠይቀዉ እንደ መፍተሄ የጠቆሙት የቡድን ስራን መጠቀም፣ ሳቢ,ያና አነቃቂ የመወያያ ርዕስ መስጠት፣ ተግባራቱን ተማሪዎች በራሳቸዉ የቃላት አጠቃቀም እንዲናገሩ ማድረግ የተሻለ እንደሆነ የጥናቱ ግኝት አመልክቷል፡፡ ይህም ሀሳብ በድሉ(2007፣89-90) ላይ ከገለፁት ገለፃ ጋር ተዛማጅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳቦች

## 5.1.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሞረትና ጅሩ ወረዳ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን መገምገም ነው ፡፡ይህን ዓብይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ አራት ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈዋል፡፡

ከተነደፉት ዓላማዎች ጋር ዝምድና ያላቸው ንድፈ ሃሳቦች በምዕራፍ ሁለት ተቀናብረዋል፡፡በምዕራፍ ሶስት ደግሞ በናሙናነት የተመረጡ ተሳታፊዎች የአመራረጥ ሂደታቸው ተብራርቷል፡፡በዚሁ ምእራፍ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉ መሳሪያዎች(የክፍል ውስጥ ምልከታ፣የፅሁፍ መጠይቅ፣ቃለ መጠይቅና ሰነድ ፍተሻ)የተዘጋጁበት ስልትና የአተናተን ዘዴያቸው ተብራርቷል፡፡

በዚህም መሰረት የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብ፣በልምምድ ጊዜ የመምህሩ ተግባር፣በአፍልቆት ጊዜ የመምህሩ ሚና እና የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተገምግሟል፡፡እነዚህን ጉዳዮች ለመገምገም የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች አተገባበርን በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በተተኳሪ መምህራን በተሞሉ የፅሁፍ መጠይቆችን እና በሚያስተምራቸው ተማሪዎች በተሞሉ የፅሑፍ መጠይቆች አማካኝነት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች እንደየዝምድናቸው በማቀናጀት በምዕራፍ አራት ተተንትነዋል፡፡በትንተናው የተገኙት ውጤቶችም እንደሚከተለው ጠቅለል ብለው ቀርበዋል፡፡

ከጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች መካከል አንደኛው በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡት የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ተግባራት የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘቡ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ስለሆነም በሰነድ ፍተሻ እንደተረጋገጠው አብዛኛው የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች እና ተግባራት የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘቡ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት

የመናገር ክሂል ትምህርት አንዳንድ ይዘቶች ከተተግባሪነትና ከአሳታፊነት አንጻር ውስንነት ያለባቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የሚረዱ ምን ምን ተግባራት እንደሚጠቀሙ መገምገም የሚል ሲሆን አብዛኛዎቹ መምህራን የተለያዩ ይዘቶችን (ክርክር ፣ ውይይት እና ጭውውት) መጠቀማቸውን የተገኘው ውጤት አመላክቷል፡፡ነገር ግን እነዚህን ይዘቶች ለማከናወን የተሰጠው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በቂ እንዳልሆነ የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤቱ አመላክቷል፡፡ ይህም በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡

ሶስተኛው የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት መምህራን ምን ምን ሁኔታዎችን እንደሚያመቻቹ መገምገም የሚል ነው፡፡ይህን በተመለከተም አብዛኛዎቹ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመናገር ክሂል ለማዳበር የአመቻችነት ድጋፍ ሲያደርጉ፣ተማሪዎች እርስ በእርስ መስተጋብር እንዲፈጥሩ ማበረታታት እና ተማሪዎች ተከታታይ ልምምድ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸታቸውን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ነገር ግን በትግበራ ላይ የጊዜ እጥረት እንዳጋጠማቸው ለማየት ተችሏል፡፡

አራተኛው የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ መምህራን የመናገር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ መለየት የሚል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተማሪዎች በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት ከንግግር መታቀብ እና ተማሪዎች የሚናገሩትን ሃሳብ ማጣት አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደሩ ጉዳዮች እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ለዚህ ችግር መምህራን እንደ መፍትሄ የጠቆሙት የቡድን ስራን መጠቀም፣ሳቢና አነቃቂ የመወያያ ርዕስ መስጠት፣ተግባራቱን ተማሪዎች በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና አገላለፅ እንዲያቀርቡ ቢደረግ የተሻለ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ሐሳቦች

በዚህ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ እንደ ችግር ለተነሱ ሃሳቦች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግብአት ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ አስተያየቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ለመምህራን**፡- የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ የተለያዩ ተግባራትን ለይተው፣በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች በተጨማሪ የተለያዩ ይዘቶችን ክፍል ውስጥ በማምጣት እንደማያስተምሩ፣እና የተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቅመው እንደማያስተምሩ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ስለሆነም መምህራን፡-

- በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ባሉ የመናገር ክሂል ትምህርት ተግባራት ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ሳቢና አነቃቂ ተግባራትን በማምጣት ማስተማር ቢችሉ፣
- የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ደረጃዎችን መጠቀም የመናገር ክሂልን ትምህርት ይዘቶችን ማስተማር ቢችሉ፣
- የመናገር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የሚያግዙ የተለያ ተግባራትን መጠቀም ቢችሉ
- የተማሪዎችን ህብረ ባህላዊና ብዝሃ አንደበትን ታሳቢ በማድረግ የተማሪዎች የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ ከፍ ማድረግ ቢችሉ፣
- **ለመርሃ ትምህርት ንድፈ ቀረፃ ባለሙያዎች**፡- የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ቢያቀርቡም ተግባራቱን ለመፈፀም የሰጡት የትምህርት ክፍለ ጊዜ በቂ አለመሆኑን ና የክፍል ውስጥ አተገባበሩን ሂደት አለማመልከታቸውን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ስለሆነም የመርሃ ትምህርት ንድፈ ቀረፃ ባለሙያዎች ፡-
- ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በመመልከት ወደፊት የመማሪያ መጻህፍትን ሲያዘጋጁ የመናገር ክሂል ትምህርትን ክፍለ ጊዜ ሁኔታ ታሳቢ አድርገው ማዘገጀት ቢችሉ፣
- የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ስርአተ -ትምህርት መቅረፅ ቢችሉ፤
- ህብረ-ባህላዊና ብዝሃ-አንደበትን ታሳቢ ያደረገ ስርአተ ትምህርት መቅረፅ ቢችሉ፤

**ለሌሎች ተመሳሳይ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኚዎች**፡-ይህ ጥናት የተካሔደው በመንግስት ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራንና በሚማሩ ተማሪዎች ላይ በሁለት ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ነው፡፡የጥናቱ ትኩረትም በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የመናገር ክሂል ይዘቶች የክፍል ውስጥ

አተገባበር ግምገማ ማድረግን የተመለከተ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አጥኚው የገንዘብና የጊዜ እጥረት ስላለበት ነው፡፡ስለሆነም በጥናቱ ያልተዳሰሱ ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ስላሉ ሌሎች ጥናት የሚያካሂዱ አጥኚዎች ፡-

- በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ መምህራን መካከል እና በሚማሩ ተማሪዎች መካከል ያለውን የመናገር ክሂል ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበርን መገምገም ቢችሉ፣
- የተማሪዎች ተሳትፎ ለመናገር ክሂል ትምህርት ያለውን ሚና መፈተሽ ቢችሉ፣

## ዋቢ ጽሑፎች


መንግስቱ ታደሰ፡፡(1997)፡፡ "በአዲስ አበባ መስተዳድር የ9ኛ ክፍልአማርኛ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ፡፡" የአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ተቋም፤ ያልታተመ፡፡

ማረው ዓለሙ፡፡ (2003) ፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡አዲስ አበባ፤ አልፋ አሳታሚዎች፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996) ፡፡ በስነ ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

---------------- ፡፡ (2007) ፡፡ በስነ ጽሁፍ ቋንቋ ማስተማር፡፡ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1981) ፡፡ስነ ልሳንና ቋንቋን ማስተማር፡፡አዲስ አበባ፤የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፤ ያልታተመ ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (2004) ፡፡የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍት፡፡ ዱባይ፤የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት፡፡

አለም እሸቱ፡፡ (1997) ፡፡ የምርምርና መሰረታዊ ዘገባ አፃፃፍ፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

አብርሃም ገ/ዮሐንስ፡፡ (2003) ፡፡ "በአፋር ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማሪያ ምርጫና አቀራረብ ግምገማ፤የአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፤ ያልታተመ፡፡

ውዳዲስ ምህረቱ፡፡ (2001) ፡፡“አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት መምህራን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች የሚሰጡትን ትኩረት ግምገማ፡፡”አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፤ ያልታተመ፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2004) ፡፡ <u>የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር፡፡</u> ሶስተኛ እትም፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጥላሁን ከበደ፡፡ (2003) ፡፡“የማዳመጥ እና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብና አተገባበር፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፤ ያልታተመ፡፡

Bailoy, K.M. (2006). Issues are teaching speaking skills to adult Esol learners. Retributed, 12, 2010 From Addis Ababa Web site.

Bygate, M. (1987).Speaking.Oxoford. OUP

Byrne, Donn.(1987) Techniques for class room Interaction.London,Longman groupUK Limited

Celece Murcia.(1991) Teaching English as a second of foreing language 2nd ed.Boston: Heinle publisher.

Creswell,John w.(2012).Research Design:Qualitative,Qantitative and Mixed methods approaches.3rd ed.SAGE Publication,Inc.

Cunnings worth, A.(1984) Evaluating and selecting EFL Teaching materials : London. Heinemann education book.

……………. (1985) choosing your course text oxford: Heinemann.

Dawson, C. (2006) practical Research methods.New Dalhi USB publishers

Dornyei, Z. (2007). Research method in applied linguistics qualitative and mixed method logies. Oxford: OUP.

Fairclough,N (2006).Discourse and social change. London: Longman.

Fayzeh shruuf (2012).Teaching and improving speaking skill.philadelphia university: The language center.

Gower, R. Phillipe, D. and Walters, S. (1995) Teaching practice hand book. Oxford. Heinemann.

Grant, N. (1987) Making the most of your text. New York: Longman Inc.

Harmer, J. (1991) the practice of English language teaching. New York: longman Group UK Ltd.

……….. (2007) the practice of English Language Teaching.(4thed) Cambridge: Cambridge university press.

Kember, D. (2009) promoting student centered forms of learning across an Entire university Higher Education.

Larsen Freeman, D. and Long, M. H. (1991) an introduction to second landuage Acquisition Research. New York: Longman Inc.

Lazar, G. (1993) Literature and language teaching. London: Longman.

Mocdonough, J, ans Shaw. C. (1995). Material and method in ELT; a teachers guide. Oxfore: black publishers.

Nunan,D.(1989).Desining Tasks for communicative class room. Cambridge: Cambridge university press.

…………. (1991) Language Teaching Methology: A text book for teachers. Practice Hall Macquarie, Sydeny.

Richards,J.C and S,T.Rodgers (1986) Approaches and methods in Language Teaching.Cambridge: Cambridge university press.

Richards, J. C and Numan, D.(1991) Second language Teacher education. Cambridge: cup.

Sahar, H.(2014) Active Learning in Kabul schools: Teachers′ view and practices.kabul,karlstads university.

Scrivener, J. (1994).Learning teacing. Oxford: Heinenan.

Sesnan , B (1997) How to teach English .oxford :cup.

Ur.P. (1996). A course In language teaching practice and theory. Cambirdige: CUP.

Widowson.H.G. (1984).Teaching language as communication. New York: OUP

------------------. (1990). Aspects of Language Teaching. Oxford: Oxforduniversity press.

Cunnings worth, A. (1984) Evaluating and selecting EFL Teachingmaterials: London. Heinemann education book.

Yamane, T. (1967). Statistics: An introductory analaysis (No.HA29 Y2 1967).

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

ጅማ ዩኒቨርስቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ፡- አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር የክፍል ውስጥ ምልከታ ማረጋገጫ ዝርዝር /Checklist/

የትምህርት ቤቱ ስም ……………………………………………………………………

በምልከታው የታየው መምህር/ት/ ኮድ …………ክፍልና ምድብ ………………..

ምልከታው የተካሄደበት ቀን ……………የተማሪዎች ብዛት ……………………..

የክፍለ ጊዜ እርዝማኔ ………………….ምልከታው የተከናወነበት ሰዓት ……………

ለረዳት ተመልካች የተሰጠ መመሪያ፡- ይህ የማረጋገጫ ዝርዝር ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ክንውኖች ጭረት /Tally/ በማደረግ ይመዝግቡ፡፡ አመዘጋገቡም ከዚህ በታች በቀረቡት ቁጥሮች ወካይነት ይሆናል፡፡

1. በጣም ከፍተኛ
2. ከፍተኛ
3. መካከለኛ
4. ዝቅተኛ

| ተ.ቁ | የምልከታ መከታተያ ነጥቦች<br><br>መምህሩ፡- | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት ያደርጋል፡፡ | | | | |
| 2 | የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቱ የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀትና የትምህርት ደረጃ ማገናዘቡን ያረጋግጣል፡፡ | | | | |
| 3 | ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀማል፡፡ | | | | |
| 4 | ተማሪዎች ለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅ መመሪያ ይሰጣል፡፡ | | | | |
| 5 | በተማሪዎችና በመምህሩ ዘንድ ግልፅ፣ እውቅና ውስን ዓላማ ይዞ ይገባል፡፡ | | | | |
| 6 | መነቃቃትን ለመፍጠር ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎችን ይጠይቃል፡፡ | | | | |
| 7 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር እንዲያደርጉ እድል በመስጠት ያለማምዳል፡፡ | | | | |
| 8 | በመናገር ልምምዱ ጊዜ ሁሉንም ተማሪዎች ያሳትፋል፡፡ | | | | |
| 9 | ተማሪዎች በሚናገሩበት ጊዜ ፍርሃት ወይም ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን ያበረታታል፡፡ | | | | |
| 10 | በልምምድ ወቅት የተማሪዎችን ስህተት ለማረም ጣልቃ እየገባ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 11 | የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ ለማዳበር መምህሩ የተጠቀሚቸው ብልሃቶች :- | | | | |
| | 11.1 ክርክር | | | | |
| | 11.2 ጭውውት | | | | |
| | 11.3 ውይይት | | | | |
| 12 | የመናገር ክሂልን ለማስተማር የቀረቡትን ይዘቶች አቅልሎ ተማሪዎችን በቀላሉና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል ዓውድ ይፈጥራል፡፡ | | | | |
| 13 | በክፍል ውስጥ ለሚቀርቡት የንግግር ማለማመጃ ተግባራት በቂ ጊዜ ይሰጣል፡፡ | | | | |
| 14 | የክፍል ውስጥ የንግግር ልምምዱ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ ያደርጋል፡፡ | | | | |
| 15 | ተማሪዎች በጥንድ ልምምዳቸዉን እንዲያዳብሩ ያደርጋል፡፡ | | | | |
| 16 | ተማሪዎች እርስ በእርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡ | | | | |
| 17 | ተማሪዎች ያለ መምህሩ ጣልቃገብነት እርስ በራሳቸዉ የሚነጋገሩበትን እድል ይፈጥራል፡፡ | | | | |
| 18 | የክፍል ውስጥ ተግባራት ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ:- | | | | |
| | 18.1 ንግግሩን ያቀረበዉ ተማሪ ራሱ ስህተቱን እንዲያይና አስተካክሎ እንዲናገር እድል ይሰጣል፡፡ | | | | |
| | 18.2 ሌሎች የክፍሉ ተማሪዎች የተማሪዉ/ዋ/ን/ ስህተት እንዲናገሩ ያደርጋል፡፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 18.3 ተማሪዋ/ዉ/ የሰራዉን/ችዉን/ ስህተት እርማትና ማስተካከያ ይሰጣል፡፡ | | | | |

# አባሪ ሁለት

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር በ2004 ዓ/ም በተዘጋጀዉ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሳሪያዎች የመማሪያ መጻህፍት፣ በመምህሩ መምሪያና በመርሃ ትምህርቱ ላይ በቀረቡት “የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ” በሚል ርዕስ ጥናት ማካሄድ ሲሆን ለዚህ ጥናት የሚያገለግሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ በጥናቱ የሚደረስበት ዉጤት በዘጠነኛ የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል አተገባበር ውጤታማነት እና ለተማሪዎች የመናገር ክሂል መዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይታመናል፡፡ ከመጠይቁ የሚገኘዉ ምላሹም ለተጀመረዉ ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ይታሰባል ፡፡ ስለዚህ ለዚህ ጥናት መሳካት የእርስዎ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ስለሆነ ይህን መጠይቅ በመሙላት የበኩልዎትን ሙያዊ ድጋፍ እንዲያደርጉልኝ ስል በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

መጠይቁን ለመሙላት ስለተባበሩኝ ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፣- በመጠየቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

ክፍል አንድ፣- የመምህራን አጠቃላይ መረጃ

ከዚህ በታች ለቀረቡት መረጃዎች ትክክለኛዉን መረጃ በተተወው ባዶ ቦታዎች ላይ ይሙሉ፡፡

1. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ……………………………….
2. ፆታ …………………..

3. የትምህርት ደረጃ ……………………..

4. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ ………………

5. የአገልግሎት ዘመን …………………………

ክፍል ሁለት፣- ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ለቀረቡት ዝርዝር መጠይቆች ምላሽ ሊሆኑ የሚችሉ አራት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ አማራጭነት ያላቸው ነጥቦች በቁጥር ተወክለው ይታያሉ፡፡ እርስዎ በጥያቄዎቹ ትይዩ የሚሰጡትን መልስ "√" ምልክት በማድረግ ያመልክቱ፡፡እነዚህ ወካይ ቁጥሮችም:-

1=ሁልጊዜ

2=አብዛኛዉን ጊዜ

3=አንዳንድ ጊዜ

4=በፍፁም የሚል የመመዘኛ ነጥቦችን የያዙ ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | የመመዘኛ ነጥቦች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | የመናገር ክሂል ትምህርትን በማስተምርበት ወቅት ዓላማውን ቀድሜ አስተዋዉቃለሁ፡፡ | | | | |
| 2 | ወደዋናው የመናገር ክሂል ተግባር ከመግባቴ በፊት ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅ እንዲነቃቁ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 3 | የመናገር ክሂል ትምህርትን በማስተምርበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የተሳትፎ እድል እሰጣለሁ፡፡ | | | | |
| 4 | የመናገር ክሂል ትምህርት ከመጀመሬ በፊት አጭርና ግልፅ መመሪያ እሰጣለሁ፡፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የንግግር ማስተማሪያ ብልሃትን (ጭውውትን)በመጠቀም ሃሳባቸውን በንግግር እንዲገልፁ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 6 | ለመናገር የማይደፍሩና ሃሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ የሚቸገሩ ተማሪዎችን በነፃነት እንዲናገሩ አበረታታለሁ፡፡ | | | | |
| 7 | የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ በጥንድ ወይም በቡድን በማደራጀት ክርክር እንዲያቀርቡ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 8 | የመናገር ክሂል ትምህርትን የማቀርበው ለደረጃው የተዘጋጀውን የመማሪያ መፅሀፍ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ | | | | |
| 9 | ተማሪዎች በጥንድ እንዲወያዩ በማድረግ የመናገር ችሎታቸው እንዲዳብር አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 10 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር ሲያደርጉ ለፈፀሙት ስህተት ወዲያው እርማት አሰጣለሁ፡፡ | | | | |
| 11 | የመናገር ክሂል ትምህርት አፍልቆቱ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን እቀይሳለሁ፡፡ | | | | |
| 12 | ለመናገር ክሂል ትምህርት የተመረጠውን ይዘት የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ መሆኑን እገመግማለሁ፡፡ | | | | |
| 13 | የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማዳበር በቡድን በማደራጀት ክርክር እንዲያቀርቡ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |

# አባሪ ሶስት

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## በተማሪዎች የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ ለማዘጋጀት መረጃ ለመሰብሰብ ነዉ፡፡ ሰከመጠይቁ የሚገኘው ውጤት ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ለጥናቱ መሳካት ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቂዎች በጥሞና አንብበው ትክክል ነው ብላችሁ ያመናችሁበትን መልስ በመስጠት እንድትተባበሩኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ማሳሰቢያ

1. በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡
2. መጠይቁን ከጓደኛ ጋር በመዎያየት መሙላት በሚሰበሰበዉ መረጃ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር በግል ይሞላ፡፡

መመሪያ አንድ፡- ቀጥሎ ለቀረቡት ክፍት ቦታዎች እንደአጠያየቃቸው ትክክለኛውን መረጃ ሙሉ፡፡

ሀ. ጾታ ……………………………

ለ. እድሜ ………………………ሐ. የክፍል ደረጃ …………………

መመሪያ ሁለት፡- ለሚከተሉት ሐሳቦች ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱን ብቻ በመምረጥ በመክበብ መልስ ስጡ፡፡

1.መምህሩ/ሯ/በአማርኛቋንቋ የመናገር ክሂል ትምህርት ክፍለ ጊዜ ዓላማውን የማስተዋወቅ ሁኔታ ምን ያህል ነው?

ሀ.ሁል ጊዜ ያስተዋውቃሉ፡፡ ሐ.አንዳንድ ጊዜ ያስተዋውቃሉ፡፡

ለ.አብዛኛውን ጊዜ ያስተዋውቃሉ፡፡ መ.በፍፁም አያስተዋውቁም፡፡

2.መምህሩ/ሯ/ የእለቱን የመናገር ክሂል ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት የማነቃቃታቸው ሁኔታ እንዴት ይገለፃል?

ሀ.ሁል ጊዜ ያነቃቃሉ፡፡ ሐ.አልፎ አልፎ ያነቃቃሉ፡፡

ለ.አብዛኛውን ጊዜ ያነቃቃሉ፡፡ መ.በፍፁም አያነቃቁም፡፡

3. መምህሩ/ሯ/ የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችን ሲያስተምሯችሁ የመማሪያ መፅሐፉን መሰረት የማድረጉ ሁኔታ ምን ያህል ነው?

ሀ.ሁል ጊዜ ሐ.አንዳንድ ጊዜ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ መ. በፍፁም መሰረት አያደርጉም፡፡

4. መምህሩ/ሯ/ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶች የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያማከለ መሆኑን ምን ያህል ይገመግማሉ?

ሀ.ሁል ጊዜ ይገመግማሉ፡፡ ሐ. አንዳንድ ጊዜ ይገመግማሉ፡፡

ለ.አብዛኛውን ጊዜ ይገመግማሉ፡፡ መ.በፍፁም አይገመግሙም ፡፡

5. መምህሩ/ሯ/ የመናገር ክሂል ትምህርትን ልምምዱ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን እንዴት ይቀይሳሉ?

ሀ.ሁል ጊዜ ሐ. አልፎ አልፎ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ መ. በፍፁም የማስተማሪያ ስልቶችን አይቀይሱም

6. መምህሩ/ሯ/የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችን (ክርክርን፣ውይይትን፣ጭውውትን ) በመጠቀም የማስተማር ሁኔታቸው እንዴት ይገለፃል ?

ሀ. ሁል ጊዜ ሐ.አንዳንድ ጊዜ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ መ.በፍፁም አይጠቀሙም

7.መምህሩ/ሯ/ የመናገር ክሂል ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት አጭርና ግልፅ መመሪያ ምን ያህል ይሰጧችኋል?

ሀ.ሁል ጊዜ ሐ. አንዳንድ ጊዜ

ለ.አብዛኛውን ጊዜ መ. በፍፁም አይተገብሩትም

8.መምህሩ/ሯ/የመናገር ክሂል ትምህርትን በሚያስተምሩበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የተሳትፎ እድል አሰጣጣቸው እንዴት ይገለፃል ?

ሀ.ሁል ጊዜ እድል ይሰጣሉ፡፡ ሐ.አንዳንድ ጊዜ እድል ይሰጣሉ፡፡

ለ. አብዛኛውን ጊዜ እድል ይሰጣሉ፡፡ መ. በፍፁም እድል አይሰጡም፡፡

9.መምህሩ/ሯ/ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎችን በነፃነት እንዲናገሩ የማበረታታት ሁኔታ እንዴት ይገለፃል?

ሀ. ሁል ጊዜ ያበረታታሉ፡፡ ሐ. አልፎ አልፎ ያበረታታሉ፡፡

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ያበረታታሉ፡፡ መ. በፍፁም አያበረታቱም፡፡

10.መምህሩ/ሯ/የመናገር ክሂላችሁን ለማሳደግ በጥንድ ወይም በቡድን በማደራጀት ጭውውት እንድታቀርቡ የሚያደርጉት እንዴት ነው?

ሀ.ሁል ጊዜ ሐ. አንዳንድ ጊዜ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ መ. በፍፁም አቅርቤ አላውቅም፡፡

11.መምህሩ/ሯ/በክፍል ውስጥ ክርክር፣ውይይት፣ጭውውት ካቀረባችሁ በኋላ ስህተታችሁን የሚያርማችሁ መቼ ነው ?

ሀ.ወዲያው ሐ.በሳምንቱ

ለ.በማግስቱ መ.በፍፁም እርማት አይሰጡንም፡፡

12.መምህሩ/ሯ/ በጥንድ እንድትወያዩና እንድትለማመዱ የሚያደርጉት ጥረት እንዴት ይገለፃል?

ሀ.ሁል ጊዜ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ሐ.አንዳንድ ጊዜ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ መ.በፍጹም ጥረት አያደርጉም፡፡

13.መምህሩ/ሯ/ክርክርን በመጠቀም የመናገር ክሂላችሁ እንዲዳብር የሚያደርጉት ጥረት እንዴት ይገለፃል?

ሀ.ሁል ጊዜ ክርክር እንድናቀርብ ያደርጉናል፡፡

ለ.አብዛኛውን ጊዜ ክርክር እንድናቀርብ ያደርጉናል፡፡

ሐ.አንዳንድ ጊዜ እንድናቀርብ ያደርጉናል፡፡

መ.በፍፁም ክርክር አቅርበን አናውቅም፡፡

# አባሪ አራት

## ጅማ ዩኒቨርስቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ፦ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን ለመገምገም የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

1. በዘጠነኛ ክፍል የመማሪያ፣ ማስተማሪያና መርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችን ቢጠቅሱልኝ? ይዘቶቹ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚያዳብሩ ናቸው?
2. መምህራን የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናሉ?
3. ለመናገር ክሂል ትምህርት የቀረበውን ይዘት የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያማከለ መሆኑን ይገመግማሉ?
4. መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርት ይዘቶችን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ጊዜ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናሉ?
5. ተማሪዎች ሃሳባቸውን በንግግር እንዳይገልፁ ያደረጉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ምንምን ናቸው? ለችግሮቹ መፍትሄ ምንድነው ይላሉ?

ውድ ጊዜዎን በመስጠት ይህንን ቃለ መጠይቅለመጠየቅ ፍቃደኛ በመሆንዎ አመሰግናለሁ፡፡